# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ማክሰኞ 83ኛ ዓመት ቁጥር 197 መጋቢት 17 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!


pepsi

# “ባለሀብቶች ሙስናን የሚጸየፍ ማኅበረሰብ ለማፍራት የድርሻችሁን ልትወጡ ይገባል”

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

ሄለን ወንድምነው



አዲስ አበባ፡- ባለሀብቶች ሙስናን የሚጸየፍና በታማኝነት ማገልገልን መርሕ ያደረገ ማኅበረሰብ ለማፍራት የድርሻችሁን ልትወጡ ይገባል ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ገለጹ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ከታማኝ ከፍተኛ ግብር ከፋዮች ጋር ሰሞኑን ባደረጉት ውይይት፤ ሙስናንና ሌብነትን በመጸየፍ በታማኝነት ማገልገል የሚችል ማኅበረሰብ ለማፍራት ባለሀብቶች የራሳችሁን ድርሻ ልትወጡ ይገባል ብለዋል።

የመንግሥት ሥልጣን ይዞ ባለሀብቶችን መኪና ግዙልኝ፣ ቤት ግዙልኝና ልጆቼን አስተምሩልኝ እያለ የሚጠይቅ ሰው እንደሠላማዊና መደበኛ ሰው መቀበሉ አግባብ አይደለም ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ይህም ሙስናን እና ሌብነትን ከማጥፋት ይልቅ ለማስፋፋት ምክንያት ይሆናል ብለዋል።

እንደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገለጻ፣ የመንግሥት ሠራተኞች ሥራቸውን በአግባቡ አይሠሩም የሚለው ሀሳብ በተደጋጋሚ ይነሳል። ይህንን ተገንዝበንና አምነን የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ለማድረግ ወደ እርምት ስንገባ በብሔር፣ በእምነት፣ በፖለቲካ እና በሌላ ነገር ያለው ዘመቻ ከባድ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

ባለሀብቶች በዚህ ጉዳይ ላይ ጨከን በማለት ሙስናን በመዋጋት ሰው በተሰማራበት መስክ ሁሉ በታማኝነት

“ባለሀብቶች ሙስናን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




## “ግብፅ በዓባይ ውኃ ሰው ሠራሽ ወንዝ እየገነባች በግድቡ ጉዳይ ኢትዮጵያን መቃወሟ ተገቢ አይደለም”

- አምባሳደር ዲና ሙፍቲ

ገጽ 4

## ኮርፖሬሽኑ የኢንዱስትሪ ፓርኮችን የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ሊፈትሽ ይገባል

- የመንግሥት ወጪ አስተዳደር እና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ

## የተከማቹ ዝቃጮችን ወደ ጥቅም ለመለወጥ እየሠራሁ ነው

- የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን

ዳግማዊት አበበ



የሺእመቤትደምሴ(ዶ/ር)



ወ/ሮ መሰረት ዳምጤ



አቶ አክሊሉ ታደሰ

አዲስ አበባ ፡- የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ከኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚወጡ ደረቅ እና ፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድን እንዲፈትሽ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግሥት ወጪ አስተዳደር እና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አሳሰበ። ኮርፖሬሽኑ በበኩሉ የተከማቹ ዝቃጮችን ወደ ጥቅም ለመለወጥ እየሠራ መሆኑን አስታውቋል።

ቋሚ ኮሚቴው የ2014/15 በጀት ዓመት የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን የኢንዱስትሪ ፓርኮች የተቀናጀ የደረቅ እና ፈሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ውጤታማነት በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ግኝቶችን በትናንትናው እለት ገምግሟል።

በወቅቱ የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የሺእመቤት ደምሴ (ዶ/ር) እንደገለጹት፤ በኢንዱስትሪ ፓርኮች ከፍሳሽ ማጣሪያ የሚወጣ ዝቃጭ በተለይም በሀዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርክ ከአምስት ዓመት በላይ በፓርኩ ውስጥ ተከማችቶ እንደሚገኝና በዝናብ ወቅት እየታጠበ ከዝናብ ፍሳሽ ጋር እንደሚወርድ ኦዲት ሪፖርቱ ያሳያል። በዚህም ከሀዋሳም ሆነ ከሌሎች ኢንዱስትሪ ፓርኮች ማጣሪያ የሚወጣው ዝቃጭ ተቀባይነት ባለው መንገድ የሚወገድበትን አልያም ጥቅም ላይ ማዋል የሚቻልበትን አሠራር መዘርጋት ያስፈልጋል።

በኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚመረቱ ምርቶች ጠቃሚ ቢሆኑም በአመራረት ሂደት ውስጥ የሚለቀቁ ደረቅና ፈሳሽ ቆሻሻዎች በሥርዓት ካልወገዱ በርካታ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ጉዳት ላይ የሚጥሉ ናቸው ያሉት ዋና ሰብሳቢዋ፤ ኮርፖሬሽኑ የማኅበራዊና የአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት ያልተደረገባቸው የማምረቻ ዘርፎች በፓርኮች አሰማርቷል፤ በመሆኑም ጥናት ያልተደረገባቸው አምራች ድርጅቶችን ወደ ፓርኮች እንዳይገቡ እና የገቡትም ጥናት እንዲደረግባቸው አሳስበዋል ።

ኮርፖሬሽኑ የኢንዱስትሪ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



## “የፓርቲው ቀጣይ ተልዕኮ በውይይት ወቅት የተነሱ የሕዝብ አንገብጋቢ ጥያቄዎች ምላሽ እንዲያገኙ ማድረግ ነው”

- አቶ አደም ፋራህ
የብልጽግና ፓርቲ ምክትል ፕሬዚዳንት

ገጽ 4







# ኮሚሽኑ ሰብዓዊ አገልግሎት እና ዘላቂ ልማት በማጣመር ፖሊሲ ቀርፃ ወደ ሥራ ገብቷል

**ሔርሞን ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- ሰብዓዊ አገልግሎትና ዘላቂ ልማትን ያጣመረ ፖሊሲ ቀርፆ ወደ ሥራ መግባቱን የኢትዮጵያ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን አስታወቀ።

በተቋሙ የሥራ አመራር ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ጌቱ ንጉሤ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳሉት፤ ኮሚሽኑ ባለፉት ጊዜያት በፊት ሲመራበት የነበረውን ፖሊሲ ለማሻሻል ሪፎርም ሲሠራ ቆይቷል። በዚህም ሰብዓዊና ዘላቂ ልማት ላይ ያተኮረ ፖሊሲ በመቅረፅ ወደ ተግባር ገብቷል።

የአደጋ ሥራ አመራር ኮሚሽን ቀደም ብሎ አደጋ ሲፈጠር ድጋፍ ማድረግ ላይ ትኩረት ይሰጥ ነበር። በመሆኑም ይህ ሚዛኑ ጠብቆ እንዲሠራ አዲስ የሪፎርም ፖሊሲ እንዲቀረፅ ምክንያት መሆኑን ተናግረዋል። የሕዝብ ቁጥር በጨመረ ቁጥር አደጋ የመስፋት ዕድል ስለሚኖር ይህን ታሳቢ በማድረግ ቀድሞ የነበረው ፖሊሲ መከለስ እንዳለበት በመታመኑ ወደ ሪፎርም መግባቱን ጠቁመዋል።

ተቋሙ አደጋ ከመከሰቱ በፊት መሠራት ያለበት ጉዳይ ለሁሉም ማኅበረሰብ እና ባለ ድርሻ አካል ማሳወቅ እንዳለበት የጠቀሱት አቶ ጌቱ፤ እሳት አደጋ እና ሌሎች



አቶ ጌቱ ንጉሤ

ሊፈጠሩ የሚችሉ አደጋዎች መለየት፣ በፋብሪካዎች አካባቢ የኤሌክትሪክ አደጋ እንዳይፈጠር ማስጠንቀቂያ መስጠት እንዲሁም መሰል ሥራዎች ቀድመው እንዲሠሩ እየተደረገ መሆኑን አብራርተዋል።

ሥራ አስፈፃሚው እንዳሉት፤ አደጋው ሲፈጠር በተቋሙ ብቻ የሚሠራ ሳይሆን ከሌሎች ተቋሞች ጋር በመጣመር የሚሠራ ነው። በመሆኑም ተቋሙ አብሮ የመሥራት ልምዶች ቢኖሩትም አሁን ላይ ግን በፖሊሲ ደረጃ ድንበር ተሻጋሪ አደጋዎችም ለመቆጣጠር የሚያስችል አሠራር እየተከተለ ነው ።

በተለይ አደጋ ከተፈጠረ በኋላ ሊሠሩ የሚገባቸው ሥራዎች እስከ አሁን እንደ ክፍተት የሚታዩ እና ትኩረት ያልተሰጣቸው መሆኑን ጠቁመዋል። ሰው በአደጋ ምክንያት ሲፈናቀል እና ቤቱ ሲፈርስ እስኪረጋጋ ድረስ የሚያስፈልገውን መጠለያ እና ምግብ ከመስጠት ባለፈ እስከ መጨረሻው ማቋቋሚያ ተሰጥቶት ወደ መደበኛ ኑሮው እንዲመለስ ለመሥራት በአዲሱ ሪፎርም ትኩረት እንደተሰጠው ጠቅሰዋል።

አዲሱ ፖሊሲ ተፈናቃዮች ቀድሞ ከነበሩበት አኗኗር በተሻለ መልኩ እንዲቋቋሙ የማስቻል አሠራር ያካተተ መሆኑን ተናግረዋል። ተቋሙ ቀደም ሲል አደጋን መሠረት ያደረገ አሠራር ይከተል የነበረ ሲሆን አሁን ላይ ግን ስጋትን መሠረት ያደረገ አሠራር መጀመሩን ገልፀዋል። ስጋትን አስቀድሞ በማሰብ አደጋን የማስቀረት ሥራ እየተሠራ እንደሆነም አስረድተዋል።



# በከተማዋ 300 ኪሎ ሜትር የውሃ ማፋሰሻ ቱቦዎች ፀድተዋል

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- በመዲናዋ 300 ኪሎ ሜትር የመንገድ ዳር ውሃ ፍሳሽ ቱቦዎችን የማስተካከልና የማፅዳት ሥራ መከናወኑን የአዲስ አበባ ከተማ መንገዶች ባለሥልጣን አስታወቀ።

የባለሥልጣኑ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ እያሱ ሰሎሞን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ የ2016 በጀት ዓመት በተጠናከረ ሁኔታ የፍሳሽ ማስወገጃ ቱቦዎችን የመጠገንና የማጽዳት ሥራ እየሠራ ይገኛል።

በመዲናዋ የውሃ ማፍሰሻ ቱቦዎች በቆሻሻ መደፈናቸውን ተከትሎ በዝናብ ወቅት ፍሳሽ ወደ መንገድ ላይ እንደሚፈስ አስታውቀው፣ እስካሁን 300 ኪሎ ሜትር የፍሳሽ ማስወገጃዎችን የማፅዳት፣ የመጠገንና በአዲስ የመተካት ሥራ መከናወኑን አስረድተዋል።

የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊው እንደገለጹት፤ ባልተገባ የመንገድ አጠቃቀም ምክንያት የመንገድ ቱቦዎች በበልግ ወቅትና በክረምት ዝናብ በሚዘንብባቸው ጊዜ ይደፈናሉ። በዚህም ከመጠገንና ከማጽዳት ሥራው በተጨማሪ የፍሳሽ ውስጥ ለውስጥ መንገዶቹን የመፈተሽ ተግባር የሚሠራ ሲሆን፤ አሁንም ሥራው እንደቀጠለ ነው ሲሉ አስረድተዋል።

አቶ እያሱ እንደገለጹት፤ ድልድዮች አካባቢ በተለይ በግንባታ ተረፈ ምርቶች የጎርፍ ማመላለሻ ቱቦዎች ይደፈናሉ። የጎርፍ አደጋ እንዳይከሰት፤ መሥሪያ ቤቱ ስጋት ያለባቸውን አካባቢዎች በመለየት እየተሠራ ይገኛል።

በዚህም ከእሳትና አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን በኩል ተለይተው የተሰጡ ቦታዎችን ባለፈው ዓመት ተጀምረው ያልተጠናቀቁትን እና አዳዲስ አካባቢዎች ላይ እየተሠራ ይገኛል ሲሉ አስረድተዋል።

እንደ አቶ እያሱ ገለጻ፤ ለመንገድ መደፈኑ ሌላው ምክንያት፤ ነዋሪዎች የመንገድ ቱቦዎቹን ከተሠሩበት ዓላማ ውጭ ስለሚጠቀሙበት ነው።

ነዋሪዎቹ ወደ ጎርፍ ማፋሰሻ ቱቦዎች ደረቅ ቆሻሻ ከመጣል እንዲቆጠቡና በተቻለ አቅም በአከባቢያቸው የሚገኙ የውሃ ማስተላለፊያዎችን እንዲያፀዱ አቶ እያሱ አሳስበዋል።

በየአካባቢው የሚገኙና የተፀዱ ቱቦዎች ዳግም እየተበላሹ በመሆኑ ይበልጥ ውጤታማ መሆን እንዳልተቻለ ጠቁመዋል።

በሌላ በኩል በክረምት ወቅትና በሌሎች ወቅቶች የመበላሸት አደጋ የገጠማቸው መንገዶች መጠገናቸውን ተናግረው፤ እስካሁን ድረስ ባለው ሂደት ከ64 ኪሎ ሜትር በላይ ጥገና ተከናውኗል ሲሉ ገልጸዋል።

በመጨረሻም ኅብረተሰቡ የሚሠሩትን የውሃ ማፍሰሻ ቱቦችንና መንገዶችን በባለቤትነት ስሜት ሊጠቀም ይገባል ሲሉ መልክት አስተላልፈዋል።



ለሚ ኮርሶ (ዶ/ር)

# በባቱ ከተማ ከሁለት ሚሊዮን በላይ ችግኞች ይተከላሉ

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- በባቱ ከተማ በዘንድሮው የአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብር ከሁለት ሚሊዮን በላይ ችግኞች እንደሚተከሉ የከተማው ግብርና ጽሕፈት ቤት አስታወቀ።

የከተማው ግብርና ጽሕፈት ኃላፊ ለሚ ኮርሶ (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ የችግኝ ዝግጅቱ እየተካሄደ ያለው በአራት የችግኝ ጣቢያዎች ሲሆን በዚህም ከ1 ነጥብ 3 ሚሊዮን በላይ ችግኞች እየፈሉ ይገኛሉ። የችግኝ ማፍላት ሥራው እስከ ግንቦት ወር ድረስ ተጠናክሮ ይቀጥላል።

በባለፈው ዓመት የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር በባቱ ከተማ ከ1 ነጥብ 5 ሚሊዮን በላይ ችግኞች መተከላቸውን የገለጹት ዶክተር ለሚ፤ የዘንድሮ ዓመት የተከላ ሥራው የአካባቢውን ሥነ ምሕዳር መሠረት በማድረግ የሚከናወን መሆኑን አብራርተዋል።

በዘንድሮው የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር በሀገር አቀፍ ደረጃ 6 ነጥብ 5 ቢሊዮን ችግኝ ለመትከል ዝግጅት እየተደረገ ነው ያሉት ዶክተር ለሚ፤ በባቱ ከተማ የችግኝ ተከላው የሚከናወንበት ሥፍራ የመለየት ሥራ በቅርቡ እንደሚጀመር ተናግረዋል። ይህም በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ቁጥጥር የሚደረግበት መሆኑንም ገልጸዋል።

እንደ ለሚ (ዶ/ር) ገለፃ፤ የባቱ ከተማ በተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና እንክብካቤ ላይ ሰፊ ሥራዎች እየተሠራ ነው። ለዚህም የከተማው አስተዳደር ለተፋሰስ ልማትና ለአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እየተንቀሳቀሰ ነው። ዛፎችን መትከል በአንድ ጊዜ ወይም በአንድ ትውልድ የሚጠናቀቅ ባለመሆኑ በትውልድ ቅብብሎሽና በእለት ተእለት ክትትል አጠናክሮ ማስቀጠል ይገባል ብለዋል።

ኢትዮጵያ ከ2011 ዓ.ም እስከ 2014 ዓ.ም ባካሄደችው የመጀመሪያ የችግኝ ተከላ መርሐ ግብርም 25 ቢሊዮን ችግኞችን መትከሏን ከግብርና ሚኒስቴር ያገኘነው መረጃ ያመለክታል።

አምና በ2015 ዓ.ም ከ7 ቢሊዮን ችግኝ በላይ የተተከለ ሲሆን በአንድ ጀምበርም ከ566 ሚሊዮን በላይ ችግኞችን መትከል ተችሏል።

ዜና

ፎቶ - ሀዱሽ አብርሃ



አቶ መሐመድ ወልዩ

# የኢትዮጵያ ባሕር በር ተጠቃሚነት ለቀጣናው ሠላምና ኢኮኖሚያዊ እድገት ወሳኝ ነው

**ቃልኪዳን አሳዬ**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- የኢትዮጵያ የባሕር በር ተጠቃሚነት ለቀጣናው ሠላም መስፈን እና ኢኮኖሚያዊ እድገት ወሳኝነት እንዳለው በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የሶማሊያ ጉዳዮች ዴስክ ኦፊሰር አቶ መሐመድ ወልዩ ገለጹ።

አቶ መሐመድ ወልዩ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ የኢትዮጵያ ባሕር በር ተጠቃሚነት ለቀጣናው ሠላም መስፈንና ለጋራ የኢኮኖሚያዊ እድገት ወሳኝ ነው። ኢትዮጵያ ሰጥቶ የመቀበል መርሕን የምትከተል ሀገር መሆኑ ለሶማሊላንድም ሆነ በቀጣናው ለሚገኙ ሀገራት በጋራ ለመበልጸግ ስምምነቱ አስቻይ ሁኔታን የሚፈጥር እንደሆነም አንስተዋል።

በርካታ ሀገራት የቀጣናውን ዙሪያ ከበውታል ያሉት አቶ መሐመድ፤ ለአብነትም የተባበሩት ዓረብ ኤምሬትስ ብቻ በአፍሪካ ቀንድ ሰባት ወታደራዊ መሠረት ያላት ሲሆን ቱርክ፣ አሜሪካ፣ ቻይና፣ ሳውዲ ዓረቢያና ሌሎችም ሀገራት ወታደራዊ መሠረት እንዳላቸው ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ በዚህ መካከል እየኖረች የባሕር በር አልባ መሆኗና የኢኮኖሚዋ 95 በመቶ የሚሆነው በጂቡቲ ላይ ብቻ ጥገኛ መሆኑ ችግር በሚፈጠርበት ወቅት ለጉዳት ተጋላጭ እንደሚያደርጋት አክለዋል።

ኢትዮጵያ ከሦስት አስርተ ዓመታት በላይ ወደብ አልባ ሆና መኖሯን የገለጹት ኦፊሰሩ፤ ከሶማሊላንድ ጋር የተደረገው ስምምነት ቀደም ቢል የሚቻል ነገር ቢሆንም አሁን ትክክለኛ ጊዜውን የጠበቀና አግባብነት ያለው ውሳኔ ነው ብለዋል።

ኢትዮጵያ ሁለቱ ሕዝቦች ታርቀው በአንድነት እንዲቀጥሉ ጥረቶች ስታደርግ እንደነበረና የሶማሊያን ሠላም ለማስጠበቅ ከፍተኛ ዋጋ መክፈሏን አስታውሰው፤ ስምምነቱም ለሁሉም ሀገሮች እድል እንጂ ጉዳት ይዞ የሚመጣ አይደለም ብለዋል።

ዲፕሎማሲ በማንኛውም ወቅት በመነጋገር በመደማመጥ የሚሠራ ሲሆን፤ የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲያዊ አካሄድ በጉዳዮች ላይ መግባባትንና መተማመንን መርሕ ያደረገ ነው፤ በሀገራቱ መካከል ሠላም እንዲሰፍን በወንበር ዙሪያ መነጋገር የግድ በመሆኑ ኢትዮጵያ ይህንንም የማታቋርጥ መሆኑን አቶ መሐመድ ጠቁመዋል።

ኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅሟን ለማስከበር የምትከተለው ገለልተኛ የዲፕሎማሲ አካሄድ ውጤት እያስገኘ ነው ያሉት አቶ መሐመድ፤ በስፋት የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ ላይ አተኩራ እየሠራች ሲሆን ኢኮኖሚ ባደገ ቁጥር አቅም ይኖራል፤ እንዲሁም በዓለም መድረኮች ላይ ተደማጭነት ያስገኛል ብለዋል።

በተለዋዋጭ ዓለም ውስጥ እየኖሩ በአንድ አካሄድ መጓዝ ተገቢ አይደለም ያሉት አቶ መሐመድ፤ በዛው ልክ ራስን በመቀየር መጓዝ ያስፈልጋል ፤ ፈጣን የቴክኖሎጂ ሽግግር ባለበት በዚህ ወቅት አዳዲስ ነገሮች የሚፈጠሩ በመሆናቸው ይህንን ከግምት ውስጥ በማስገባት ሁሉም ዜጋ ለሀገሩ ጥቅም ሲል ዲፕሎማት መሆን እንዳለበት አንስተዋል።

ዲፕሎማሲ የሁሉም ዜጋ ድምር ውጤት ነው፤ በዚህም በተወሰኑ ሰዎች ብቻ የሚሠራ ባለመሆኑ የዲጂታል ዲፕሎማሲን በማስፋት የተደረሰው ስምምነት እንዲጸናና ኢትዮጵያ ማግኘት ያለባትን ጥቅም እንድታገኝ በዓለም አቀፋዊና በቀጣናዊ ተቋማት ውስጥ የሚሠሩ ኢትዮጵያንን ጨምሮ ሁሉም ዜጋ ሊረባረብ እንደሚገባ አስገንዝበዋል።

# የኮሪደር ልማቱ ዘመናዊ ከተማን ለመገንባት ያስችላል

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- በአዲስ አበባ ከተማ እየተገነባ የሚገኘው የኮሪደር ልማት የከተማዋን ለውጥ በማረጋገጥ ዘመናዊ ከተማን ለመገንባት የሚያስችል መሆኑን የኢትዮጵያ አርክቴክቶች ማኅበር ፕሬዚዳንት አቶ ሀብታሙ ጌታቸው ተናገሩ።

ኮሪደሩ ከመንገድነቱ ባሻገር እይታን ሳቢ በማድረግ የከተማዋ መግቢያና መውጫ ያማረና የተስተካከለ እንዲሆን የሚያደርግና የከተማዋን ገጽታ የሚያስተካክል ነው ያሉት አቶ ሀብታሙ፤ ለበርካታ ችግሮች መነሻ የሆነው የትራፊክ ፍሰትንም መስመር ለማስያዝ የሚጠቅም ይሆናል ብለዋል።

በአሁኑ ወቅት ያሉት አብዛኛዎቹ የከተማዋ መንገዶች መናበብ የማይታይባቸው፤ የት ጀምረው የት እንደሚጠናቀቁ የማይለዩም ናቸው ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ የሚገነቡት የእግረኛና የብስክሌት መንገዶችም ፅዱና ነፋሻማ አካባቢ በመፍጠር የኅብረተሰቡን ጤና ለመጠበቅ ጠቃሚ እንደሚሆኑ ጠቁመዋል።

ከተሞች እያደጉና እየተስፋፉ የሕዝብ ቁጥርም እየጨመረ ሲመጣ ሁሉም ነገር የሚገኝባቸው የከተማ እምብርት የሚባሉ ነገሮች እየቀሩ ይመጣሉ። በአንጻሩ የተለያየ ማኅበረሰቡ የሚያስፈልጉትን አገልግሎቶች ተደራሽ የሚያደርጉ ማዕከላት በተለያዩ ቦታዎች በቅርበት እንዲኖሩ ይጠበቃል። አሁን እየተሠሩ ያሉ ኮሪዶሮችም እነዚህን ለማገናኘት የሚጠቅሙ ይሆናል። እነዚህም ዘመናዊ መንገዶች አሏቸው በሚባሉ ከተሞች የሚተገበር ነው ብለዋል።

አቶ ሀብታሙ እንደገለጹት፤ ባደጉት ሀገራት ያሉ ከተሞች ስማቸው ሲጠራ በሕሊና የሚፈጠር የየራሳቸው መለያ አላቸው። በተጨማሪ ከተሞች በአሁኑ ወቅት በእድገት ውድድር ወስጥ ይገኛሉ። ለምሳሌ ኬንያ በቅርቡ ትልቁን ሕንጻ ለመገንባት ዲዛይን አስመርቃለች።




ይህም ሆኖ ለማንኛውም የከተማ ልማት ሥራ የነዋሪዎችንና የባለሙያዎችን ሀሳብ ማካተት እንደሚገባም አቶ ሀብታሙ ጠቁመዋል።

በሌላ በኩል የሕንጻዎች ከፍታና ብዛት ሲጨምር ከፍሳሽ፣ ከኤሌክትሪክና ከውሃ አቅርቦት ጋር የተያያዙ የመሠረተ ልማት ፍላጎቶች ስለሚጨምሩ ይህንን ለመቋቋም በሚያስችል መልኩ ትኩረት የሚፈልግ ይሆናል ብለዋል።

በግንባታው ወቅትም እንደ ቅርስ የተያዙ ቦታዎችን መጠበቅ የሚገባ ሲሆን ይህ እንኳ ለልማት ሲባል የግድ መነሳት ቢኖርበት ዘመኑ በደረሰበት መንገድ በቴክኖሎጂ ዶክመንት አድርጎ መዝግቦ ማስቀመጥ ይጠበቃል ሲሉም አክለዋል።

በተጨማሪም የሚሠሩ አዳዲስ ግንባታዎችም የከተማዋ ነዋሪ የኔ ነው ብሎ እንዲቀበል የድሮ ነገሮችን የሚመስሉ ግን አዳዲስ ግንባታዎችን መሥራት የሚቻልበት እድልም አለ ያሉት አቶ ሀብታሙ፤ በመሆኑም እነዚህን ነገሮች በማድረግ የከተማዋን ነዋሪ በኮሪዶር ልማቱ ተሳታፊም ተጠቃሚም ማድረግ ይቻላል ብለዋል።

ፎቶ፡ በረሀነ ታደሰ




# የድሬዳዋ የመጠጥ ውሃ ማስፋፊያ ፕሮጀክት ግንባታ እየተፋጠነ ነው

**ተስፋ ፈሩ**

<u>ድሬዳዋ</u>፡- የድሬዳዋ የመጠጥ ውሃ ማስፋፊያ ፕሮጀክት ግንባታ እየተፋጠነ እንደሚገኝ የከተማ አስተዳደሩ አስታወቀ።

የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ውሃና ፍሳሽ ባለሥልጣን ሥራ አስኪያጅ መሐመድ ሙሴ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በሁለት ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ብር እየተገነባ የሚገኘው የድሬዳዋ የመጠጥ ውሃ ማስፋፊያ ፕሮጀክት ሙሉ በሙሉ በከተማ አስተዳደሩ በጀት የሚሠራ ነው።

ፕሮጀክቱ በከተማ አስተዳደሩ አቅም ከመገንባቱ ጋር ተያይዞ ደረጃ በደረጃ እየተሠራ እንደሚገኝ የጠቆሙት ሥራ አስኪያጁ፤ ከ230 እስከ 530 ሜትር ጥልቀት ያላቸው የ12 ጉድጓዶች ቁፋሮ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ተጠናቋል ብለዋል።

ቀጥሎም 57 ኪሎ ሜትር የሚደርስ የቧንቧና የመገጣጠሚያ ግዢ ተፈፅሞ፣ ከሐምሌ ወር 2015 ዓ.ም. ጀምሮ የኤሌክትሮ መካኒካል እና የሲቪል ሥራ ግንባታው በአንድነት እየተከናወነ እንደሚገኝ ገልፀዋል።

"በድሬዳዋ ከውሃ እጥረት ባለፈ እየቀረበ የሚገኘው ውሃ በአነስተኛ መጠንም ቢሆን 'ካልሽዬም ባይካርቦኔት' የተባለ ንጥረ ነገር ስላለው መጠነኛ የጥራት ችግር አለበት" ያሉት አቶ መሐመድ፤ የከተማዋ አስተዳደሩ በራሱ አቅም በጀት መድቦ ችግሩን ለመቀነስ ትልቅ እገዛ እያደረገ እንደሚገኝ ተናግረዋል።

የግንባታ የፕሮጀክት ጽሕፈት ቤት ኃላፊው አቶ አብዱላዚዝ መሐመድ በበኩላቸው፤ የድሬዳዋ የመጠጥ ውሃ ማስፋፊያ ፕሮጀክት የከተማዋን የውሃ ተደራሽነት አሁን ካለበት 50 በመቶ ከ20 እስከ 25 በመቶ ከፍ ያደርገዋል ተብሎ ይጠበቃል ብለዋል ።

ከ12ቱ ጉድጓዶች ወደ ማዕከሉ ውሃ የመሰብሰቢያ መስመሮች ሥራ 33 በመቶ መከናወኑን ጠቁመው፣ የሚሰበሰበው ውሃ የሚጠራቀምበት ቋት 5 ሺ ሜትር ኪዩብ (5 ሚሊዮን ሊትር) ውሃ የመያዝ አቅም እንዳለው ተናግረዋል።

በአጠቃላይ ከ12ቱ ጉድጓዶች በሰከንድ 490 ሊትር ውሃ ይሰበሰባል ያሉት ኃላፊው፤ ውሃው የሚጠራቀምበት ጉድጓድ ዳገታማ ስፍራ ላይ መገኘቱ ለከተማዋ የተለያዩ አካባቢዎች ውሃን በመሬት ስበት ኃይል ለማዳረስ እንደሚያስችል አንስተዋል።

የፕሮጀክቱ አማካሪ ጌታቸው ወርቁ፣ ፕሮጀክቱ ድሬዳዋ ከደረቅ ወደብና ነፃ ንግድ ቀጣና መገኛነቷ እንዲሁም ወደፊት ከምታደርገው መስፋፋት ጋር ተያይዞ ለሚኖረው ከፍተኛ የውሃ ፍላጎት ከአሁኑ ዝግጅት በማድረግ በቂ አቅርቦት እንዲኖር ለማድረግ ታልሞ እየተገነባ እንደሚገኝ ገልፀዋል።

የድሬዳዋ የመጠጥ ውሃ ማስፋፊያ ፕሮጀክት ግንባታ የተጀመረው ከሁለት ዓመታት በፊት ሲሆን፣ በአሁኑ ወቅት አጠቃላይ የግንባታው አፈፃፀም 50 በመቶ መድረሱ ተነግሯል።

# “የፓርቲው ቀጣይ ተልዕኮ በውይይት ወቅት የተነሱ የሕዝብ አንገብጋቢ ጥያቄዎች ምላሽ እንዲያገኙ ማድረግ ነው”

- አቶ አደም ፋራህ
የብልጽግና ፓርቲ ምክትል ፕሬዚዳንት

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- የብልጽግና ፓርቲ አመራሮችና አባላት ቀጣይ ተልዕኮ በውይይት ወቅት የተነሱ የሕዝብ አንገብጋቢ ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ እንዲያገኙ ማድረግ መሆኑን የፓርቲው ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ አደም ፋራህ ገለጹ።

የአዲስ አበባ ከተማ ብልጽግና ፓርቲ ቅርንጫፍ የማጠቃለያ ኮንፈረንሱን ባከናወነበት ወቅት አቶ አደም ፋራህ እንደገለጹት፤ የፓርቲው አመራሮችና አባላት ቀጣይ ተልዕኮ በቅርቡ በሁሉም አካባቢዎች በተደረጉ ውይይቶችና ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከተለያዩ ክልሎች ከተወጣጡ የኅብረተሰብ ክፍሎችና የሃይማኖት አባቶች ጋር በመከሩበት ወቅት የተነሱ አንገብጋቢ የሕዝብ ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ እንዲያገኙ ማድረግ ነው።

በሁሉም መድረኮች የተነሱትን ጥያቄዎች ፓርቲው በአምስት መልኩ እንደሚያይ የገለጹት አቶ አደም፤ የመጀመሪያውና ትልቁ ከሠላም አኳያ የተነሳ መሆኑን ገልጸዋል፤ በውይይቱ በሀገሪቱ የተሟላ ሠላም መረጋገጥ እንዲችል መንግሥት ሚናውን እንዲጫወትና ሕዝቡም ኃላፊነቱን ለመወጣት ዝግጁነቱን አሳይቷል ነው ያሉት።

ፓርቲው በሀገሪቱ ዘላቂ ሠላምን ለማረጋገጥና ግጭቶችን በሠላም ለመቋጨት በተጀመረው አግባብ ጥረቱን አጠናክሮ በመቀጠል መፍትሔ የሚገኝበትን ሁኔታ ለመፍጠር አቅጣጫዎች አስቀምጧል ብለዋል።

እንደ አቶ አደም ገለጻ፤ ግጭት ባለባቸው አካባቢዎች ዜጎች ማኅበራዊ ሠላማቸውን አጥተው ልጆቻቸውን ማስተማርና የእለት ተግባራቸውን ማከናወን አልቻሉም። ችግሩ እንዲፈታ የሚፈልጉ የሀገር ሽማግሌዎች፣ የሃይማኖት አባቶችና ታዋቂ ግለሰቦች ተሳትፈውበት መንግሥትም የድርሻውን ተወጥቶ ችግሮች በሠላም የሚፈቱበት ሁኔታ መፈጠር አለበት።

ከዚህ ቀደም ግጭቶቹን ለመፍታት የተለያዩ ጥረቶች መደረጋቸውን አስታውሰው፤ ለኢትዮጵያ መልካም በመመኘት የሚንቀሳቀሱ እንዳሉ ሁሉ በአደራዳሪነት ስም ጉዳዩ ይበልጥ እንዲወሳሰብ ለማድረግ የሚጥሩ አካላት በመኖራቸው ሕዝቡ እድል ሊሰጣቸው እንደማይገባ አስገንዝበዋል።

የፀረ ሠላም ኃይሎች የሕዝቡን መብትና ጥቅም ማስከበር ሳይሆን የሕዝቡን ማኅበራዊ እረፍት በመንሳት እኩይ ዓላማቸውን የማሳካት ፍላጎት እንዳላቸው ያነሱት አቶ አደም፤ መንግሥት የተጀመረውን ጥረት አጠናክሮ በመቀጠል መፍትሔ እንደሚሰጥ ተናግረዋል።

ሀገሪቱ ከግጭትና ጦርነት አዙሪት ነፃ እንድትወጣ የተጀመረው አካታች ሀገራዊ ምክክርና የሽግግር ፍትሕ ሥርዓት በተሟላ መልኩ እንዲተገበር መደገፍ እንደሚያስፈልም የገለጹት አቶ አደም፤ ኅብረ ብሔራዊ አንድነትን በማጠናከር የግጭት መንስኤዎችን ከምንጫቸው ማድረቅ እንደሚገባ ጠቁመዋል።

በውይይቱ ወቅት ጎልቶ የወጣው ሁለተኛው የሕዝቡ አንገብጋቢ ጥያቄ የኑሮ ውድነት ነው ያሉት አቶ አደም፤ ለዚህም እንደሀገር ያሉትን አቅሞች በመጠቀምና በየአካባቢው የተጀመሩ መነሳሳቶችን ተግባራዊ በማድረግ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ ትኩረት እንደሚደረግበት አመልክተዋል።

እንዲሁም አምራቹና ሸማቹን የሚያገናኙ ሥራዎችን በመሥራት ዜጎች መሠረታዊ ሸቀጦችን በተመጣጣኝ እንዲያገኙ በማድረግ የግብይት ሥርዓቱን የማሻሻል ተግባር እንደሚከናወን አክለዋል።

እንደ አቶ አደም ንግግር፤ ሦስተኛው የሕዝቡ ጥያቄ የሥራ እድል ፈጠራ ነው። ለዚህም በዜጎች ላይ የአስተሳሰብ ለውጥ በማምጣት ሥራ ፈላጊዎች እድሎቻቸውን በአግባቡ እንዲጠቀሙ ማድረግ ሲሆን፤ ለሥራ ፈጣሪዎች ከኢንተርፕራይዞች ጀምሮ ድጋፍ በመስጠት ራሳቸውን የሚችሉበትን ሁኔታም ለመፍጠር ታስቧል።

አራተኛው በአገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ እንደሆነ የጠቆሙት አቶ አደም፤ ለዚህም ፓርቲው የአገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓቱን በቴክኖሎጂ በመደገፍ እንዲዘምን በማድረግ፣ ግልጸኝነትና ተጠያቂነት እንዲሰፍን ለማስቻል አቅጣጫ ማስቀመጡን ተናግረዋል።

አምስተኛው ዋነኛ የሕዝቡ ጥያቄ የመሠረተ ልማት መስፋፋት ሲሆን ለዚህም በጀት ተይዞላቸው በአፈጻጸም ጉድለት እየተጓተቱ ያሉ ፕሮጀክቶችን የማፋጠን ሥራ ይሠራል፤ እንዲሁም በእቅድ ተይዞ በቂ በጀት የሌላቸውን የልማት ሥራዎች ለማጠናቀቅ ሕዝቡንና የልማት አጋሮችን በማስተባበር የዜጎች ጥያቄ ምላሽ እንዲያገኝ ትኩረት ይደረጋል ሲሉ አቶ አደም አመላክተዋል።

# “ግብፅ በዓባይ ውኃ ሰው ሠራሽ ወንዝ እየገነባች በግድቡ ጉዳይ ኢትዮጵያን መቃወሚ ተገቢ አይደለም”

አምባሳደር ዲና ሙፍቲ

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- ግብፅ ኢትዮጵያን ሳታስፈቅድ በዓባይ ወንዝ አማካኝነት ሰው ሠራሽ ወንዝ እንደምትገነባው ሁሉ በዓባይ ግድብ ጉዳይ ኢትዮጵያን መቃወሟ ተገቢ አይደለም ሲሉ አምባሳደር ዲና ሙፍቲ ገለጹ።

አምባሳደር ዲና እንደገለጹት፤ ግብፅ ያለ ኢትዮጵያ ፍቃድ ወንዝ መሥራቷ ኢትዮጵያ የዓባይን ግድብ ለመሥራት የእነርሱን ፈቃድ መፈለግ አለባት የሚለው አቋም የተሳሳተ መሆኑን ያሳያል።

እንደ አምባሳደር ዲና ገለጻ፤ ከዚህ ቀደም ግብፅ በዓባይ ውኃ ስትጠቀም ቆይታለች። በርካታ የልማት ሥራዎችን መሥራት ችላለች። ይህ የሆነው ከኢትዮጵያና የላይኛው ተፋሰስ ሀገራት በተገኘ አይደለም። ያለ ፈቃድ የራሷን ወንዝ እስከገነባች ድረስ በዛው ልክ ኢትዮጵያንም በዓባይ ግድብ ጉዳይ መቃወምና መከራከሯ ተገቢ አይደለም።

ኢትዮጵያ የምትከተለው መርሕ የዓባይ ወንዝን የተፋሰሱ ሀገራት የመጠቀም መብት አላቸው የሚለውን ነው ያሉት አምባሳደር ዲና፤ ይህ ውኃ አብዛኛው የሚመነጨው ከኢትዮጵያ በመሆኑ ሌሎች የተፋሰሱ ሀገራት መጠቀም የለባቸውም የሚል አቋም የላትም ሲሉ ገልጸዋል። ከዚህ ቀደምም ስታራምደው የነበረው አቋም ይህንኑ ነው ብለዋል።

በኢትዮጵያ በኩል እየተራመደ ያለው አቋም ኢትዮጵያ ከውኃ የመጠቀም ሙሉ መብት አላት የሚለው ሲሆን፤ ይሄንን ከታችኛውም ሆነ ከላይኛው የተፋሰሱ ሀገራት ፍቃድ ማግኘት እንደሌለባት ግብፅ የኢትዮጵያን ፍቃድ ሳትፈልግ በዓባይ ውኃ አማካኝነት የምታከነውናቸው ሥራዎች ማሳያ መሆናቸውን ተናግረዋል።

ግብፅ ወንዙን ለመሥራት ኢትዮጵያን እስካላስፈቀደች ድረስ፤ ኢትዮጵያ ደግሞ በራሷ ሀብት ላይ ግድብም ሆነ ሌላ ነገር ለመሥራት የታችኛውንም ሆነ የላይኛውን ተፋሰስ ሀገራት ፍቃድ ማግኘት የለባትም የሚለውን ነገር እያጎላው መሆኑን ያሳያል ነው ያሉት።

ለወንዙ እንደ ምንጭነት ከምትጠቀማቸው መካከል የዓባይ ወንዝ እንደመሆኑ በግድቡ ላይ የምታንጸባርቃቸው ክርክሮችና ጫናዎች የራሷን ጥቅም ብቻ ከማየት የመጣ ነው በሚለው ሀሳብ የሚስማሙት አምባሳደር ዲና፤ ከመጀመሪያውም ጀምሮ የኢትዮጵያ ትክክለኛው አቋም የዓባይ ተፋሰስ ሀገራት የመጠቀም መብት እንዳላቸው የሚያሳይ እንደሆነ አመላክተዋል።

ኢትዮጵያ በግድቡ ላይ የምትሠራው የታችኛውን ተፋሰስ ሀገራት አይጎዳም የሚል እምነት እንዳለም ጠቅሰዋል። እንደውም ጤናማ የሆነ ጠቀሜታ ማግኘት እንደሚችሉና ግድቡ አንዳንዶችን ከጎርፍ እንደሚታደግ ገልጸዋል።

ግድቡ ውኃን በላይኛው ደጋ ክፍል ስለሚያከማች የውሃ ትነት አያጋጥምም የሚል አቋም እንዳለ፤ ከዚህ



ሁሉም ተጠቃሚ መሆናቸውን፤ ውኃው ለኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ሰጥቶ የሚያልፍ እንጂ ምንም የሚቀነስ ነገር የለም የሚለውን ኢትዮጵያ በተለያዩ መድረኮች ስታንጸባርቅ መቆየቷን አንስተዋል።

ይሄ ሁሉ እያለ ሰው ሠራሽ ወንዝ ለመሥራት የምትጣጣር ሀገር ኢትዮጵያን ደግሞ ለመብራት ኃይል ግድብ መሥራት የለባትም ብላ መሞገት ተገቢ እንዳልሆነ ተናግረዋል።

## “ባለሀብቶች ሙስናን...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ማገልገል አለበት የሚለውን መርሕ ማስተማር ይጠበቅባችኋል ሲሉ አስገንዝበዋል።

በሀገሪቱ መሠረተ ልማት መገንባትና ዘላቂ ሠላም መስፈን አለበት የተባለው ተገቢ መሆኑን አንስተው፤ ከመንግሥት ወገን በሚገኝ ገቢ ብቻ ሠላምን ማስፈንና መሠረተ ልማትን መገንባት የማይታሰብ በመሆኑ ሁሉም ሰው የድርሻውን ሊወጣ እንደሚገባም አስታውቀዋል።

ወደ ተለያዩ ሀገራት የተሰደዱ ባለሀብቶችን ወደ ሀገር ተመለሱ ስንል የሠራነው ሥራ ይታወቅብናል ብለው ስለሚፈሩ መመለስ አይፈልጉም ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ እኛ እንደመንግሥት ከዚህ ክልል ጋር ግጭት ስላለ ውጡ ብለን ከሀገር ያስወጣነው አንድም ባለሀብት የለም ሲሉ ተናግረዋል።

ግብርን በሚመለከት ኢትዮጵያ ከግብር ማግኘት የሚገባትን ገቢ ካላገኘች የምናስበውን ብልጽግና እውን ማድረግ አንችልም ብለን በርካታ ሕጎችን የማሻሻልና ከቴክኖሎጂ ጋር የማገናኘት ሥራ ሠርተናል ብለዋል።

በዚህም ግብር ከፋዮች ከአመራርና ከባለሙያ ጋር ሳይገናኙ በዲጂታል የክፍያ አማራጮች መክፈል እንዲችሉ መደረጉን አንስተዋል። ባለፉት አራት ዓመታት የግብር ገቢን ለማሳደግ በተሠሩት ሥራዎች የፌደራል ግብር ከፋዮችን ከ40 ሺህ ወደ 61 ሺህ ማሳደግ መቻሉንም አመልክተዋል።

እንደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ማብራሪያ፣ በ2010 ዓ.ም የኢትዮጵያ መንግሥት የሰበሰበው 235 ቢሊዮን ብር በወቅቱ ከነበረው ጥቅል ሀገራዊ ምርት አንጻር ከ10 በመቶ በላይ ነው። በ2015 በጀት ዓመት ደግሞ 557 ቢሊዮን ብር ተሰብስቧል።

ይህ ቁጥር ባለፉት ዓመታት በጥሬ ገንዘብ ከተሰበሰበው በእጥፍ የጨመረ ቢሆንም አሁን ላይ የሀገሪቱ ጥቅል ሀገራዊ ምርት ዘጠኝ ትሪሊዮን ብር እየተጠጋ ነው። ከዘጠኝ ትሪሊዮን 11 በመቶ እንኳን ግብር ብንሰበስብ አንድ ትሪሊዮን ብር መሰብሰብ አለብን ብለዋል። ለዚህ የግብር አስተዳደራችንን በማሻሻል ሁሉም በታማኝነት ግብሩን መክፈል አለበት ሲሉ ተናግረዋል።

ሕግን አክብሮ ተገቢውን ግብር መክፈልን ባሕል ያደረገ ማኅበረሰብ አለመኖሩ፣ ግብርን ማጭበርበር እንደሌብነት አለመታየቱ፣ የተጭበረበረን ግብር የማስከፈል አቅም አለመኖሩ እንዲሁም ግልጽ አሠራር ያለውና ሰዎች ግብራቸውን በታማኝነት እንዲከፍሉ የሚያበረታታና ብቃት ያለው ተቋም አለመፍጠራችን ኢትዮጵያ ከግብር ማግኘት የሚገባትን ገቢ እንዳታገኝ ምክንያት መሆኑን አስረድተዋል።

በኢትዮጵያ ጥቅል የሀገራዊ ምርት 30 በመቶ ድርሻ ያለው እንዲሁም ትራክተር፣ ማዳበሪያ፣ የግብርና ባለሙያ፣ ምርጥ ዘርና ሌሎች ግብዓቶችን የሚጠይቀው ግብርና ምንም አይነት ግብር አይከፈልም ሲሉ ለአብነት አንስተዋል።

የሀገር ውስጥ ብድርን በሚመለከት መንግሥት ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 2015 ዓ.ም ብቻ ለግሉ ሴክተር የሚሰጠውን ብድር ከ45 በመቶ ወደ 86 በመቶ እንዲሁም ከ236 ቢሊዮን ብር ወደ 545 ቢሊዮን ብር ማሳደጉን ገልጸው፤ ይህ የሚያሳየው የሚሰጠው ብድር ማነሱን ሳይሆን የእናንተ ፍላጎት ማደጉን ነው ብለዋል።

የውጭ ሀገሩን ብድር በሚመለከት ደግሞ ከለውጡ በፊት 58 በመቶ የሚሆነው የኢትዮጵያ ጥቅል ሀገራዊ ምርት እዳና አራጣ መሆኑን አስታውሰው፤ ላለፉት ዓመታት ለመድኃኒት የሚወጣውን ሳይጨምር ኢትዮጵያ ከምታመነጨው የውጭ ምንዛሪ በአማካኝ ሁለት ቢሊዮን ዶላር፣ ለነዳጅ አራት ቢሊዮን ዶላር እና ለማዳበሪያ አንድ ቢሊየን ዶላር መክፈሉን ገልጸዋል።

ባለፉት አራትና አምስት ዓመታት ኢትዮ ቴሌኮምና አየር መንገድ የከፈሉትን እዳ ሳይጨምር መንግሥት ዘጠኝ ነጥብ ዘጠኝ ቢሊዮን ዶላር እዳ መክፈሉን ገልጸዋል።

ባለፉት አምስት ዓመታት 75 ቢሊዮን ዶላር የተለያዩ ምርቶችን ወደ ሀገር ለማስገባት ወጪ ተደርጓል። ከዚህ ውስጥ እዳን፣ ነዳጅንና ማዳበሪያን ሳይጨምር 65 በመቶ ለግል ሴክተሩ ተሰጥቷል። መንግሥት የዛሬ ሦስት ዓመት ለግሉ ሴክተር ሲያቀርብ የነበረው የብርና የውጭ ምንዛሪ መጠን በእጥፍ አድጓል። የሚቀርበው ብድርና የውጭ ምንዛሪ በቂ ነው ከተባለ ግን በቂ አይደለም። አሁንም በትብብር መሥራትን ይጠይቃል ነው ያሉት።

በኢትዮጵያ ካለው አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን መኪና 85 በመቶ የሚሆነው የግሉ ሴክተር ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በቀጣይ የነዳጅ ወጪን ለመቀነስ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን ለማስፋፋት ተባብረን መሥራት ይገባል ብለዋል።

በአዲስ አበባ በተጀመረውን የኮሪደር ልማት የሚፈርሱ ቤቶች፣ አጥሮችና የመሥሪያ ቤቶች ዘር፣ እምነት፣ ብሔርና ፖለቲካን መሠረት ያደረጉ ሳይሆን ኢትዮጵያንና አዲስ አበባን ለመገንባት ዓላማ ያደረገ መሆኑን መረዳት እንደሚገባ አስገንዝበዋል።

## ኮርፖሬሽኑ የኢንዱስትሪ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ሰብሳቢዋ፤ ኮርፖሬሽኑ በደብረብርሃን እና በባሕርዳር ኢንዱስትሪ ፓርኮች የፍሳሽ ማጣሪያ ግንባታ ሥራዎች በዚህ ዓመት እንደሚጠናቀቅ በያዘው እቅድ መሠረት አጠናቆ ሥራ እንዲያስጀምር አሳስበዋል ።

የፌዴራል ዋና ኦዲተር ወይዘሮ መሠረት ዳምጤ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ ኮርፖሬሽኑ ያሉበትን በርካታ የክዋኔ ኦዲት ግኝቶች በድርጊት መርሐግብሩ መሠረት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ሊሠራባቸው ይገባል ብለዋል ።

ኮርፖሬሽኑ ለፍሳሽ ቆሻሻ ማጣሪያ ያወጣው ወጪ ከባለሃብቶች ለፍሳሽ ማከሚያ ከሰበሰበው ገቢ ጋር ሲነጻጸር ለፍሳሽ ማጣሪያ ከፍተኛ ወጪ እያወጣ በመሆኑ ተገቢውን ታሪፍ እንዲያዘጋጅ አሳስበዋል ።

የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ አክሊሉ ታደሰ በበኩላቸው፤ ሀዋሳን ጨምሮ በኢንዱስትሪ ፓርኮች ተከማችተው የሚገኙ ዝቃጮችን ወደ ማዳበሪያና ወደ ግንባታ ግብዓት በመቀየር መልሰው ጥቅም ላይ እንዲውል እየተደረገ ይገኛል። በዚህም ፓርኮቹን ፅዱና አረንጓዴ የማድረግ ሥራዎች ማከናወን ተችሏል ሲሉ ገልጸዋል።

ዋና ሥራ አስፈጻሚው፤ የፍሳሽ ማስወገጃ ታንከሮች በሁሉም የኢንዱስትሪ ፓርኮች ደረጃ መገንባታቸውን ገልጸው፤ አልሚዎችም ጊዜያዊ ማጣሪያዎችን እንዲገነቡ መደረጉን ጠቁመዋል።

የደብረብርሃን እና ባሕርዳር ኢንዱስትሪ ፓርኮች የፍሳሽ ቆሻሻ ማጣሪያ ግንባታ በቅርቡ ተጠናቆ ወደ ሥራ እንደሚገባ የገለጹት ዋና ሥራ አስፈጻሚው፤ እስካሁንም ወደ ሥራ እንዳይገቡ የፀጥታ ችግር እና የበጀት እጥረት ምክንያት መሆናቸውን አንስተዋል ።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ለኢትዮጵያ ዋጋ ከሚከፍሉት ጋር መተባበር ይገባል!

ኢትዮጵያ በዋጋ የፀናች፤ በመስዋዕትነት የዘለቀች፤ በሕዝቦች ዘርፈ ብዙ ተጋድሎ ከፍ ያለ ስምና ዝናን የተጎናጸፈች ሀገር ናት፡፡ ምድረ ቀደምትነቷ፤ የነፃነትና ሉዓላዊነት ገጿ፤ የእኩልነትና ኅብር መልኳ፤... የተሳሉት በሕዝቦቿ ብርቱ ጥረትና ትጋት፤ በጀግኖቿ ከፍ ያለ መስዋዕትነት ታግዞ ነው፡፡

ይሄ ስምና ዝና፤ ነፃነትና ክብር፤ በጥቅሉም የኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያውያን ገድል ታዲያ እንደ ትናንቱ ሁሉ ዛሬም በአያሌ ፈተናዎች የታጀበ ስለመሆኑ እሙን ነው፡፡ በተለይ በዘመናዊው ዓለም ውስጥ ዘመኑን መስለና ከዘመኑ እውነታ ጋር ተላምዳ ለመሻገር፤ ክብርና ነፃነቷንም በዛው ልክ ለማዝለቅ በምታደርገው ሂደት ውስጥ አያሌ ፈተናዎችን መጋፈጧ የግድ ሆኗል፡፡

ዛሬ ዛሬ ከሀገር ይልቅ ክልልና መንደር፤ ከሕዝብ ይልቅ ብሔርና ቡድን የሚያስጨንቃቸው፤ ሆዳቸው ክብራቸው የሆኑ ኃይሎች እዚህም እዚያም እያቆጠቆጡ ይገኛል፡፡ እነዚህ ኃይሎች ደግሞ ኢትዮጵያ እንደ ሀገር፤ ኢትዮጵያውያንም እንደ ሕዝብ በሚያደርጉት የሠላም፣ የልማትና የሁለንተናዊ ብልጽግና እውን መሆን ሂደት ላይ ከፍ ያለ ጥላን ማጥላታቸው አይቀርም፡፡

ከዚህ አኳያ ሕዝቦች የኢኮኖሚ ነፃነት ናፍቀው ልማትና ሁለንተናዊ ብልጽግናቸውን እውን ለማድረግ በሚተጉበት በዚህ ወቅት፤ ጦርነት እና ግጭትን አማራጭ ያደረጉ እኩያን ተበራክተው ይታያሉ፡፡ እነዚህ ኃይሎች ደግሞ ሠላም አይጥማቸውም፤ ምክንያቱም የሚያተርፉት ከግጭትና ጦርነት ስለሆነ፡፡

ለዚህም ሲሉ በሕዝቦች መካከል መቃቃርን ለመፍጠር ይሠራሉ፤ ቂምና ቁርሾን ያስፋፋሉ፤ የበዳይና ተበዳይነት እሳቤን ለማስረጽ ይተጋሉ፡፡ በዚህም፣ ሕዝቦች ቅሬታ እንዲሰማቸው፤ የተበዳይነት ስሜት እንዲፈጠርባቸው፤ ከልማት ሂደቱ የራቁ ሆነው እንዲሰማቸው የሚያደርጉ አያሌ ተግባራትን ይፈጽማሉ፡፡

እናም የመሠረተ ልማቶችን ከማውደም ጀምሮ የዜጎችን ሃብት ንብረት የመዝረፍ፣ ዜጎችን የማፈናቀል፣ በዜጎች ላይ የአካልም የሕይወትም ጥቃት የማድረስ ከፋታቸውን ይገልጣሉ፡፡ ይሄ ደግሞ ዜጎች ሠላምና ደኅንነት እንዳይሰማቸው፤ ፍቅርና አብሮነት እንዳይኖራቸው፤ ከመንግሥት ጋርም ወደ አለመተማመን እንዲገቡ እና የእነሱን እኩይ ሃሳብ እንዲላበሱ ማድረጊያ ስልታቸው ነው፡፡

ይሄ የሀሳብም፣ የተግባርም መንገድ ደግሞ ሀገርንም፣ ሕዝብንም ዋጋ እያስከፈለ፤ መንግሥትም በሙሉ አቅሙ ወደ ልማት ሥራዎች እንዳያተኩር እያደረገ ይገኛል፡፡ ለዚህም ነው በአንድ በኩል ሰላም በማስከበር፤ በሌላ በኩል የልማት ተግባራትን በማከናወን ሁሉን አቀፍ ጥረት እየተደረገ ያለው፡፡፡

እነዚህን የሕዝብን ሠላም እና ሁሉን አቀፍ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በመንግሥት ለሚከናወኑ ሥራዎች አቅም ከመሆን አኳያ ደግሞ በርካታ አካላት የማይተካ ዋጋ እየከፈሉ ይገኛሉ፡፡ የፀጥታ አካላት፣ ባለሃብቶች፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ የሃይማኖት አባቶች፣ ወጣቶች፣ ምሑራን፣ እና ሌሎች የዴሞክራሲ ተቋማት በዚህ ረገድ ከፍ ያለ ሥራን እየሠሩ መሆኑ እሙን ነው፡፡

ለምሳሌ፣ የፀጥታ ኃይሎች ሚና ሲታይ፤ ኢትዮጵያ እንደ ሀገር፣ ኢትዮጵያውያንም እንደ ሕዝብ ነፃና ሉዓላዊ ሆነው፤ ሠላማቸው ተጠብቆ በሙሉ የደኅንነት ስሜት ወደ ልማታቸው እንዲያተኩሩ የማድረጉን ከፍ ያለ ድርሻ እየተወጡ ይገኛል። በዚህ በኩል የመከላከያ ሠራዊቱ፣ የደኅንነት ተቋሙ እና የፖሊስ ኃይሉ ቀዳሚ ናቸው፡፡

እነዚህ አካላት፣ ለኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያውያን ሕልውና እና ሁለንተናዊ ብልጽግና ተኪ የሌለው ሕይወታቸው እስከመስጠት የሚደርስ ዋጋን እየከፈሉ የኖሩ፤ የሚኖሩም ናቸው፡፡ በተለይ የመከላከያ ሠራዊቱ ከቤት ወጥቶ፣ ከቤተሰቡ ርቆ፣ በዱር በገደሉ ውሎ እያደረ፤ ብርድና ሓሩሩ ሳይበግረው፤ ጋራና ሸንተረሩ ሳያዝለው ለሀገሩ ክብር፣ ለሕዝቡም ደኅንነት እየከፈለው ያለው ዋጋ ከማንም ልብና አዕምሮ የሚፋቅ አይሆንም፡፡

ለዚህም ነው፤ የመከላከያ ሠራዊቱ መልኩ ኢትዮጵያዊ፣ ገጹም ኢትዮጵያ ነው የሚባለው፡፡ ለዚህም ነው መከላከያ ሠራዊቱን መደገፍ፣ ከመከላከያ ሠራዊቱ ጎን መቆም፤ ኢትዮጵያን እንደ መደገፍ፣ ከኢትዮጵያ ጎን እንደመቆም የሚታየው፡፡ ምክንያቱም ይሄ ኃይል ስለ ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያውያን ሲል የሚሰስተው አንዳችም ዋጋ የለምና ነው፡፡

ከሰሞኑ በመከላከያ ሠራዊት እውነተኛ ታሪክ ላይ ተመሥርቶ "ስለ እናት ምድር" የተሰኘ ፊልም ተመርቋል፡፡ ይሄ ፊልም ደግሞ ከበዛው የመከላከያ ሠራዊቱ ተጋድሎና የልዕልና መገለጫዎች መካከል በወፍ በረር ለማሳየት የተሞከረበት እንጂ፤ ሙሉ እሱነቱን ያሳያል ተብሎ የሚወሰድ አይሆንም፡፡ ምክንያቱም ሁነቱ ውቅያኖስን በጭልፋ እንደማለት ነውና፡፡

ለምሳሌ፣ የመከላከያ ሠራዊቱ ባለፉት ዓመታት አያሌ ተጋድሎዎችን ፈጽሟል፤ በዚህ ረገድ በሰሜኑ ጦርነት ወቅት የፈጸመው ገድልና ሥነምግባር የተሞላበት ተግባር ተጠቃሽ ነው፡፡ በዛው ልጅ የጦር አቅሙንም ገንብቷል፡፡ ዛሬም ቢሆን በዚሁ መልኩ ተጋድሎውን እየፈጸመ፤ አቅሙንም እያሳደገ ያለ ተቋምና ሠራዊት ነው፡፡

ለዚህም ነው፣ በፊልሙ ምርቃት ላይ ተገኝተው መልዕክት ያስተላለፉት ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ፣ የተመረቀው ፊልም እዚሁ የመከላከያ ሠራዊቱ ተግባር ላይ የተመሠረተ ስለመሆኑ ከመግለጽ ባሻገር፤ መከላከያ ሠራዊቱ የኢትዮጵያ ሠላምና ደኅንነት የመጨረሻው ምሽግ ስለመሆኑ አፅንዖት ሰጥተው፤ ከመከላከያ ሠራዊት ጋር መቆም፣ ከኢትዮጵያ ጋር መቆም መሆኑንም የተናገሩት፡፡

መከላከያ ሠራዊትን የመሰሉ ሁሌም ታሪክ የሚሠሩ ኃይሎች ደግሞ፣ ስለ ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያውያን ሲሉ ዋጋ የሚከፍሉ ናቸው፡፡ ከእነዚህ ኃይሎች ጎን መቆም እና አብሮ መሥራት ደግሞ ከኢትዮጵያ ጎን መቆምና ለኢትዮጵያ መሥራት ከመሆኑም ባሻገር፤ ከፍ ያለ ክብርን የሚያጎናጽፍ ሠናይ እሴትም ነው፡፡ እናም ስለ ኢትዮጵያ ሲባል ለኢትዮጵያ ዋጋ ከሚከፍሉት ጋር መተባበር ይገባል!


**አዲስ ዘመን**

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፦ epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፦ 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፦ ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ሕዝባዊ ውይይቶች ለዘላቂ ሀገራዊ ሠላም

ፍሬሕይወት አወቀ

በአንድ ሀገር የተረጋጋ ፖለቲካና ኢኮኖሚ መገንባት የሚቻለው የተረጋጋ ሠላምና ፀጥታን ማስፈን ሲቻል መሆኑ ሳይታለም የተፈታ ነው። የተረጋጋ ሠላምና ፀጥታን ለማስፈን ደግሞ የአንበሳውን ድርሻ የሚወስደው መንግሥት ቢሆንም፤ ሕዝብም እንደ ሕዝብ በሀገሪቱ ሠላምና ፀጥታ እንዲሰፍን ያለው ድርሻ ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለም፡፡ ለዚህም ነው ሁሉም ሰው ሊባል በሚችል ደረጃ ለሠላሙ ዘብ ሲቆም የሚታየው፡፡ ብዙዎች ከቤታቸው አልፎ ጎረቤታቸው፣ አካባቢያቸውና ሀገራቸው ሠላም ውላ ሠላም እንድታድር የየዕለት ልመናና ጸሎታቸው ነው፡፡

በተቃራኒው ደግሞ ከብዙ በጥቂቱ የሁሉ ነገር መሠረት የሆነውን ሠላም ለማደፍረስ እንቅልፍ የሚያጡ ኃይሎች አሉ፡፡ በእነዚህ ኃይሎች እኩይ ተግባር የተነሳ በተለያዩ ሕዝቦች ሠላምና መረጋጋት እንዲርቃቸውና በአንጻሩ ጦርነት፣ የእርስ በርስ ግጭት፣ ሽብርተኝነትና ወንጀል ተንሰራፍቶ የሰዎች ዕለታዊ እንቅስቃሴ እንዲገታ ሲያደርጉ ኑሯቸው እንዲታወክ፣ የሚሊዮኖች ሕይወት እንዲጠፋና ንብረት እንዲወድም ሆኗል፡፡ እየሆነም እያየን ነው፡፡ በሠላም እጦት ምክንያትም በዓለም አቀፍ ደረጃ በየዓመቱ ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ ለኪሳራ እንደሚዳረግ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

ኢትዮጵያም ከዓለም የተለየች አይደለችምና ዓለም ባለፈባቸው ምቹና ምቹ ባልሆኑ መንገዶች ሁሉ ለማለፍ ትገደዳለች፡፡ ለዚህም ነው ኢትዮጵያ በተለያየ ጊዜ የተለያዩ ችግሮች ሲገጥሟት የሚስተዋለው፡፡ ያም ቢሆን ታዲያ ኢትዮጵያዊ ብልሃትና እሴቶቿን ተጠቅማ የገጠሟትን ችግሮች በመልካም እሴቶቿ ስትፈታ ኖራለች። ዛሬም እየሆነ ያለው ይኸው ነው፡፡ በሀገሪቱ ሊሆኑ አይደለም ሊታሰቡ የማይችሉ ድርጊቶች ተከናውነው አይተናል፡፡ በድርጊቱም ብዙዎች ታመዋል፡፡ ያም ቢሆን ‹‹ዓይን አያየው፤ ጆሮ አይሰማው ነገር የለም›› በማለት በኢትዮጵያዊ ጨዋነት አይተን እንዳላየን ሰምተን እንዳልሰማን ቻል አድርገን አልፈናል፡፡

‹‹ሁሉም ያልፋል...›› እንዲል ታላቁ መጽሐፍ፣ ኢትዮጵያውያን ብዙ ሺህ መከራዎችን ችለው ማሳለፍ የቻሉት አንድም ፈሪሃ እግዚአብሔር ያላቸው በመሆናቸው ሁለትም የበዙ መልካም እሴቶች ያሏቸው በመሆናቸው ነው ቢባል ስህተት የለውም፡፡ ይሁንና ኢትዮጵያ ለሠላም የሚተጉ ውድ ልጆች እንዳሏት ሁሉ፤ ሠላሟ እረፍት የሚነሳቸውና ሰላም በማጣቷ ብዙ የሚያተርፉ የሉም ማለት አይቻልም፡፡

በብዙዎች ዕንባ፣ ኀዘንና ሰቆቃ የሚደሰቱ፣ ኪሳቸው ሞልቶ የሚትረፈረፍና ኑሯቸው እንደ ጠዋት ፀሐይ የሞቀና የደመቀላቸው ብዙዎች ናቸው፡፡ የሀገር ሠላም ሲናጋ ንጹሐን ለከፋ የሕይወት ምስቅልቅሎሽ ቢጋለጡም፣ በሰዎች ስቃይ ለሚያተርፉ ግን ሠርግና ምላሽ ይሆናል፡፡ ስለዚህ ሠላምን አጥብቆ መሻት ለተግባራዊነቱም በብዙ መትጋት ከእያንዳንዱ ዜጋ ይጠበቃል፡፡

እርግጥ ነው ኢትዮጵያ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ በአሁን ወቅት ለሠላም ያላትን ዝግጁነት በተለያየ መንገድ እየገለጸች ትገኛለች፡፡ ለዚህም ቀዳሚውን ድርሻ የሚወስደው መንግሥት እንደመሆኑ መንግሥት ሠላም በሰዎች ሕይወት ውስጥ ያለውን ትልቅና ውድ ዋጋ በመረዳት ከትናንት እስከ ዛሬ እጆቹን ለሠላም ዘርግቷል። አሁንም ለሠላም የተዘረጉ እጆቼ አይታጠፉም በማለት የሀገር ሠላም እንዲጸና ሕዝቦች በአንድነት ተዋደውና ተፋቅረው በሠላምና በጋራ እንዲኖሩ የተለያዩ ጥረቶችን እያደረገ ይገኛል፡፡

ከሰሞኑ በሀገሪቱ ሲካሄዱ የነበሩት ሕዝባዊ ውይይቶች ለዚህ ዋነኛ ምስክሮች ናቸው፡፡ ሰሞነኛው የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በሀገሪቱ ከሚገኙ የተለያዩ አካባቢዎችና ቤተ ዕምነቶች ከተውጣጡ የኅብረተሰብ ክፍሎች ጋር ያደረጓቸው ሕዝባዊ ውይይቶች ሀገሪቱ ለምትፈልገው ዘላቂ ሠላም፣ መረጋጋትና አንድነትን ለማምጣት ያላቸው ፋይዳ እጅግ የጎላ ነው፡፡ በመሆኑም መሰል ሕዝባዊ ውይይቶች መለመድ ያለባቸውና ይበልጥ ሊጎለብቱ የሚገባቸው እንደሆኑ ይታመናል፡፡

ችግሮችን ለመፍታት መወያየትና መነጋገር ቀዳሚው አማራጭ መሆን እንዳለበት ከሰሜኑ ጦርነት መማር ችለናል፡፡ በተለይም መንግሥት ታች ካለው የማኅበረሰብ አካል ጋር በሀገሪቱ አሉ የተባሉ ችግሮችን ለመፍታት በሚያስችል መንገድ መወያየት መጀመሩ ትልቅ ውጤት ነው፡፡ መንግሥት ከተለያዩ የሃይማኖት አባቶች ጋር እንዲሁም ከተለያዩ የማኅበረሰቡ ክፍሎች ከተወጣጡ አካላት ጋር ውይይት ማድረጉ ሀገሪቷ አሁን ያለችበትን ነባራዊ ሁኔታ ፍንትው አድርጎ ማየትና መረዳት የሚያስችለው በመሆኑ ትልቅ ዕድል ይፈጥርለታል፡፡

መንግሥት ችግሮችን በውይይት ለመፍታት እንዲችል ውይይትን በማኅበረሰቡ ዘንድ ማዳበር ከማስቻሉ ባሻገር ዘላቂ ሠላምን ለማረጋገጥ ያለው አማራጭ ከፍተኛ እንደሆነም ይታመናል፡፡ ዘላቂ ሠላምን ለማረጋገጥ ችግሮችን ከማኅበረሰቡ ከራሱ ማድመጥ ችግሮችን በማስወገድ ረገድ ተጨባጭ ለውጦችን ማምጣት የሚችልና የሠላም በሮች የሚከፈቱበትን ዕድል የሚያሰፋ ነው፡፡

ሰሞንኛ ሕዝባዊ ውይይቶች መረጃን መሠረት ያደረጉና መሬት ላይ ያለውን እውነታ መሠረት ያደረጉ በመሆናቸው ችግሮቹን በግልጽ ለመረዳት አበርክቷቸው የጎላ ነው። በሀገራችን ባልተለመደ ሁኔታ መንግሥት ሕዝባዊ ውይይቶችን ማድረጉ በብዙዎች ዘንድ የሚደገፍ ከመሆኑም በላይ ተጨባጭ ለውጦችን ማምጣቱም አይቀሬ ነው፡፡ ውይይቱ በተለይም በመንግሥትና በሕዝብ መካከል ያለውን ግንኙነት የሚያጸና፣ ግልጸኝነትን የሚያመጣና ችግሮችን እያጠበበ የሚሄድ እንዲሁም ችግሮቹ እንዴት መፈታት እንዳለባቸው አቅጣጫ የሚያሳይ እንደሚሆን ይታመናል፡፡

መረጃን መሠረት ያደረገው ይህ ሕዝባዊ ውይይት፣ ለመንግሥትና ለመንግሥት ከፍተኛ አመራሮች በሙሉ የማንቂያ ደውል የመሆን ዕድሉም የሰፋ ነው፡፡ እስካሁን የተካሄዱት ሕዝባዊ ውይይቶችም የችግሮቹ መነሻ ከየትም ይሁን ከየት እውነታውን ፍንትው አድርገው ማሳየት የሚችሉ በመሆናቸው ለዜጎች ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት ፋይዳቸው የጎላ ነው፡፡ ሕዝባዊ ውይይቱ በሰላምና ደኅንነት፣ በመልካም አስተዳደር፣ በማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ ትኩረቱንን ያደረገ በመሆኑ መንግሥት ቃል ገብቶ ያልፈጸማቸውን ተግባራት ሕዝቡ ለምን ሲል መጠየቅ እንዲችል ዕድል ፈጥሮለታል፡፡

በመጨረሻም፣ ለሠላም ትልቅ ድርሻ ያላቸው ሕዝብና መንግሥት መቀራረብ፣ መነጋገርና መደማመጥ ከቻሉ፤ ኢትዮጵያ የራቃትን ሠላም መልሳ ታገኛለች፡፡ ሕዝብና መንግሥት ተቀራርበውና ተማምነው መሥራት ከቻሉ ዘላቂ ሠላምን ማስፈን ይቻላል፡፡ ዘላቂ ሠላምን ማምጣት ከተቻለ ደግሞ ሀገራዊ ብልጽግናን ለማረጋገጥ ከባድ አይሆንም፡፡ ለዚህ ሁሉ ታዲያ ሕዝባዊ ውይይቱ የታለመለትን ዓላማ ማሳካት የግድ ይለዋል፡፡ መንግሥት ከሕዝባዊ ውይይቱ ያገኘውን ግብዓት ተጠቅሞ መሥራት ያለበትን የቤት ሥራ እንደየቅደም ተከተሉ መሥራት የሚጠበቅበት ሲሆን፤ በተለይም ሕዝብ በመንግሥት ላይ አመኔታ እንዲያጣ የሚየሩ አሻጥሮችን መለየትና ከስሩ መንቀል ከመንግሥት የሚጠበቅ ጥልቅ ሥራ ነው፡፡ አበቃን!

# ነፃ ሃሳብ

## ከፍታችን ከሀገር ለመቀበል ሳይሆን ለሀገር በመስጠት ውስጥ የሚመጣ ነው

ቴልጌልቴልፈልሶር (የኩሽ አሽከታብ)

ሀገር የግለሰቦች የሀሳብ፣ የአብሮነት፣ የምክክርና የአብሮ መቆም ውህድ ናት፡፡ ሀሳብና አብሮነትን በቀየጠ በዚህ የሰው ለሰው መስተጋብር ውስጥ የምንፈልጋትን ሀገር መፍጠር እንችላለን። አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ ሀገራችን ከእኛ፣ እኛም ከሀገራችን የምንፈልገው ነገር አለ፡፡

ይሄ መሻት የሰጥቶ መቀበል ወይም ደግሞ ‹GIVE AND TAKE› የሚለውን ሳይንሳዊ እሳቤ የታከከ ነው፡፡ አሁን ባለው ወቅታዊ ሁኔታ ሀገራችን ከእኛ ምንድነው የምትፈልገው ብሎ መጠየቅ? ለጋራ መጠቃቀሙ የመጀመሪያው ምዕራፍ ነው፡፡ ሀገራችን ምን እንደምትፈልግ ካልጠየቅንና ካልመለስን፤ በተዘዋዋሪ እኛ ምን እንደሚያስፈልገን አልተረዳንም ማለት ነው፡፡

በዚህ ሀሳብ ውስጥ የሚገለጸው ደግሞ የሀገር ፍላጎት የሕዝብ ፍላጎት ነው፡፡ የሀገር መሻት የትውልዱ ዋነኛ ጥያቄ ሆኖ የሚገለጽ ነው፡፡ ለዚህ ሀገርና ሕዝብን አቅፎ ለያዘው የጋራ ጥቅም እንደቅድመ ሁኔታ የሚወሰደው ‹ሀገር ከዜጎቿ ምን ትሻለች?” የሚለው፤ ወይም ደግሞ ከፍ ብዬ እንደገለጽኩት ባለው ወቅታዊ ሁኔታ “የሀገራችን መሻት ምንድነው?” የሚለው ይሆናል፡፡

ይሄ ጥያቄ ደግሞ “ሀገሬ ለእኔ ምን አደረገችልኝ ሳይሆን እኔ ለሀገሬ ምን አደረኩላት?” የሚለውን የአሜሪካውን የቀድሞ ፕሬዝዳንት የጆሴፍ ኬኔዲን አባባልና ፍልስፍና ታኮ የሚመጣ ይሆናል፡፡ ከዚህ አኳያ ስለሀገርና ሕዝብ ከተነገሩና እውነትነት ሆነው ከፊት ከተቀመጡ አባባሎች ውስጥ ቀዳሚው ‹ሀገሬ ለእኔ ሳይሆን እኔ ለሀገሬ ምን አደረኩ? ብሎ መጠየቅ እንደሆነ በብዙዎች ዘንድ የታመነ ነው፡፡

ብዙዎቹ በኢኮኖሚና በፖለቲካ ብሎም በሕዝባዊ አንድነት ሀያልነትን የገነቡ ሀገራት ባልዳበረ ተፈጥሮ ሀብትና በውስን የሰው ኃይል እንዴት ገናናነትን አገኙ ብለን ስንጠይቅ የምናገኘው የመጀመሪያ መልስ ከሀገር የሚቀበሉ ሳይሆኑ ለሀገር የሚሰጡ መሆናቸውን ነው፡፡ ከሀገር መቀበልና ለሀገር መስጠት አንድ የሚመስል ግን ደግሞ እጅግ የሰፋ ልዩነት ያለው አስተሳሰብ ነው፡፡

እናም ይሄ በቀድሞውም ሆነ አሁን ባለው ትውልድ መካከል የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ፣ የሉአላዊነት፣ የዲፕሎማሲ ልዩነትን የፈጠረ አስተሳሰብ ነው፡፡ ያለመጠራጠር አሁን ላለው ዓለም እድገትና ስልጣኔን የሰጠና የነጠቀ የሁለት ጎራዎች የተለያየ ምልከታ ነው፡፡ ብዙ ሀገራት ከራስ በፊት ሀገርን በማስቀደም፣ ከራስ ፍላጎት የሕዝብን ፍላጎት በማስቀደም ከሰጪነት ወደ ተቀባይነት ዞረዋል፡፡ በተቃራኒው እንደ እኛ ያሉ ሀገራት ከሀገር በፊት ራስን ባስቀደመ ፖለቲካና ማኅበረሰባዊ ልምምድ ያልሰጠነውን ለመቀበል እጃችንን የዘረጋን ነን፡፡

ዋናውና መሀሉ ሀገር በመገንባት ሂደት ውስጥ ከፊት የሚመጣው ልዩነት ይሄ ነው፡፡ ያልሰጡትን መጠበቅ ለድህነትና ለኋላ ቀርነት ብሎም ለተቃርኖ መንገድ የሚከፍት የተሳሳተ አስተሳሰብ ነው፡፡ በዚህ ውስጥ ወድቀን ሀገራችንን ስንተች፣ ያለፈውን ስንወቅስ መጥተናል፡፡ ለአለውና ለሚኖረው ምቹና አስፈላጊዎች መሆን አቅቶን፣ ሰጥቶ ከመቀበል ይልቅ ተቀብሎ ለመስጠት የተሰለፍን ነን፡፡

በዚህ ይሄ ተቀብሎ የመስጠትን እንጂ የሰጥቶ መቀበልን መርህ እሳቤ ላይ አደገኛው ነገር የአመለካከት ክፍተቱ ብቻ ሳይሆን፤ በልምምድ የመጣ የረጅም ጊዜ ሂደት መሆኑም ነው፡፡ በሁሉም መስክ ላይ ማለት ይቻላል ከእኛ ምን እንደሚጠበቅ አለማወቃችን ሀገራችንን ያቀነጨረ ድርጊት ነው ባይ ነኝ፡፡ የሀገር እድገት፣ የማኅበረሰብ ለውጥ የሕዝብ ሀሳብና ድርጊት የተውጣጣበት

> **ሀገርን ታሳቢ ባደረገ መልኩ ሀሳብ ሰጥተን ሀሳብ ስንቀበል፣ የእርቅና አስታራቂ ሀሳቦችን ስናቆራኝ የበለጠ እንድንሰጥና የበለጠ እንድንቀበል ተአማኒነትን ይፈጥርልናል**

ነው፡፡ ጥያቄችን ሰላም ከሆነ፣ ለልማትና ለአንድነት ጽኑ መሻት ካለን ለነዛ የሚሆን የሀሳብና የአብሮነት ልዕልና ልናዳብር ይገባናል፡፡

የሀገር ሰላም የእኔና የእናንተ ተግባቦትና ምክክር ነው፡፡ ልማትና እድገትም ከእኛው በእኛ የሚመጣ እንጂ በተዐምር የሚሆን አይደለም። በእኔ ምልከታ እስካሁን ድረስ ለሀገራችን የሰጠናት ነገር የለም፡፡ ሆኖም ያልሰጠነውን ለመቀበል የሌለንን ለመውሰድ ግን በብዙ ትችትና ሙግት የቆምን ነን፡፡ የአሜሪካንን የታሪክና የስልጣኔ ሰነድ ብታገላብጥ በወርቅ ቀለም ደምቆ የምታገኙት የመጀመሪያው እውነት እኔ ለሀገሬ ምን አደረኩ? የሚል ጥያቄ ያዘለ ግን ደግሞ ለሁሉም ሕዝባዊ መሻት መልስ የሚሰጥን እውነታ ነው፡፡

ይሄ እሳቤ ማንንም ከምንምነት የሚያነሳ፣ ከብርቱ እጆችና ከበሳል ጭንቅላቶች በላይ ኃይል ያለው ነው፡፡ የቱንም ያህል በርትተን የምንሰጠው ሳይኖረን ጠባቂዎች ብቻ ከሆንን ኃይላችን ትርጉም አይኖረውም፡፡ የሰጥቶ መቀበል መርህ ከገባን ግን ምንም ያክል ተስፋቢሶች ብንሆን ያለንን በመስጠት፣ የሚጠበቅብንን በማድረግ ሂደቱን መጠበቅ እንጀምራለን፡፡ አሁን ባለው የሀገራችን ነባራዊ አውድ ስር እንደሰላምና ልማት ያሉ የሚነሱ ብዙ ሕዝባዊ መሻቶች አሉ፡፡ እኚህ መሻቶች የጋራችን ከመሆናቸው እኩል በጋራ የሚተገበሩ የጋራ ውጤቶች እንደሆኑ ሊገባንም ይገባል፡፡

ፍላጎታችን ሰላም ከሆነ ለሰላም የሚሆኑ ሀሳቦችን ከማመንጨት ጀምሮ ለተግባቦትና አብሮ ለመስራት ራሳችንን ማዘጋጀት ቀዳሚውና ለሀገር ሰጥተን ከሀገር የምንቀበለው የሰላም መሻት መሆን ይችላል፡፡ ፍላጎታችን የፖለቲካ ጉዳይ፣ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ጥያቄ ከሆነም መጀመሪያ ከእኛ የሚጠበቅ ለውይይትና ለምክክር ልብና አእምሮውን መክፈት ፊተኛው ሀቅ ነው፡፡ ሰጥቶ መቀበል ማለት በልዩነቶቻችን ላይ የበላይ መሆን ማለት ነው፡፡ ትናንሽ የሀሳብ፣ የታሪክ ልዩነቶች እንዳያቃቅሩንና ወደጦርነት እንዳይወስዱን ሰላም አመንጪ በሆነ ሀሳብ ማጥበብ ማለት ነው፡፡

የትኛውም ሕዝባዊ ጥያቄ በሰጥቶ መቀበል መልስ ማግኘት ይችላል፡፡ ለዚህ ደግሞ ምክክር ቀዳሚው መሳሪያ ሲሆን፤ ይሄን እንዲከውን የተሰየመው ብሄራዊ ምክክር ኮሚሽንም ላለፉት ዓመታት ሰላምና አብሮነትን ማዕከል ባደረገ መልኩ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል፡፡ ከኮሚሽኑ ዓላማዎች ውስጥ አንዱ በሰጥቶ መቀበል የተበላሹ ትርክቶችን ማስተካከል፤ ያደፉ ታሪኮችን ማጽዳትና የተጣመሙትን ማቃናት ይገኝበታል፡፡

ይሄን ዓላማ ሰንቆ ስራውን እውን ሲያደርግ ደግሞ በእርቅና በይቅርታ ከምንም በላይ ደግሞ በኢትዮጵያዊነት ወግና ልማድ የነበረንን የአብሮነት ትስስር የመመለስ ግብ አለው፡፡ ሂደቱ ሰጥቶ መቀበል የጎላበት ለመሆኑ እንደማሳያ የሚነሳው የሀሳብ ቅብብሎሽ፣ ነጻ መድረክና ገለልተኛነት ያለው መሆኑ ነው፡፡ ሀገርን ታሳቢ ባደረገ መልኩ ሀሳብ ሰጥተን ሀሳብ ስንቀበል፣ የእርቅና አስታራቂ ሀሳቦችን ስናቆራኝ የበለጠ እንድንሰጥና የበለጠ እንድንቀበል ተአማኒነትን ይፈጥርልናል፡፡

እናም መልካም እሴቶችን ስናጎላ፣ የቀደሙ የጎብረብሄራዊ ገድሎቻችንን ስንዘክር፣ አብሮነታችንን ስናውጅ ለሀገር እየሰጠን ነው፡፡ ተምረን ለቁም ነገር ስንበቃ፣ ወልደን ስንስም፣ ሰርተን ስንከብር፣ በፍቅርና በአብሮነት ስንጠያየቅ በምትኩ ሀገር እየሰጠችን ነው፡፡ ይሄ እውነታ በአንድ ቃል ቢገለጽ ሰጥቶ መቀበል ይሆናል፡፡ ለሀገራችን የሰጠናትን ሀገራችን መልሳ ሰጠችን ማለት ነው፡፡

በየትኛውም ሀገር ሰጥቶ መቀበል አንድ አይነት ትርጉም ነው ያለው፡፡ እየሞትንና እየገደልን፣ እየሰረቅንና እያጭበረበርን፣ እየተገፋፋንና እየተጠላላን ሀገራችን የምትሰጠን ሰላም የላትም። በቋምና በቀል፣ በዘርና በብሄር ተቧድነን ሀገራችን የምትሰጠን ወንድማማችነት የለም። ያንጻባረቅነው ነው የሚንጸባረቅልን፡፡ ሀገር ማለት ሰው ነው የሚለው አባባል ከዚህ እውነታ የተጸነሰ ነው፡፡ የምንፈልገው በእኛ ውስጥ ነው ያለው፡፡ ለምንፈልገው የሚሆን ትስስርና ቁርኝትን ከፈጠርን ይሆንልናል፡፡ ያቃተን ለምንፈልገው ነገር ዋጋ መክፈል ነው፡፡ ያልቻልነው በመነጋገር የሚያግባቡንን ሀሳብና ተግባቦት መፍጠር ነው፡፡

የሆነው፣ እየሆንን ያለውና ወደፊትም የምንሆነው እርሱ ነው፤ እጣ ፈንታችን፡፡ የነበረውን ካስታወስን ለዛሬ ሰላም እና አንድነት ማጣታችን ቁርሾ የተቀመጠበት፣ ትርክት የተተረከበት እንደሆነ ማስታወስ ይቻላል፡፡ እየሆንነው ያለውን መዘከር ካስፈለገ ደግሞ በትላንት ትርክቶች ዋጋ እየከፈልን ያለንበትን ሁኔታ ማስታወስ ሌላው እውነታ ነው፡፡ ወደፊት የምንሆነውም እጣ ፈንታችን ወሳኝ ሆኖ ከፊት የሚቀመጥ ነው፡፡ ወደ መፍትሄው ከመጣን ትላንትን በዛሬ መሻር ነገን በአሁን ማቅናት የሚል ይሆናል፡፡

ትላንትን በዛሬ መሻር አሁን ላሉብን ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ ምስቅልቅሎች እልባት የሚሰጥ የመፍትሄ አቅጣጫ ነው፡፡ ትላንትን በዛሬ ካልሻርን ነገን የጋራችን፣ ነገን የኢትዮጵያ ማድረግ አንችልም፡፡ በመጣንበት የዘርና የጎሳ ክፍፍል፣ በእኔ እና በየአንተ ንትርክ ትውልዱን ሀገር እና ወገን እናሳጣዋለን፡፡ ይሄ ደግሞ በራስ ላይ እሳት እንደማንደድ የሚቆጠር በሀገር ላይ የሚያስጨክን ድርጊት ነው፡፡ ራሳችንን ነጻ በማውጣት ለሕዝብና ለትውልድ የምንተርፈው ከእዳ ወደ ምንዳ፣ ከፈተና ወደልዕልና፣ ከአንባጓሮ ወደአብሮነት በሚወስድ የእርስ በእርስ ጎዳና ላይ ስንቆም ነው፡፡

ዛሬን የትላንቱን በይቅርታ ለማለፍ፣ ነገን ፍቅር ለመቀበል፣ የእርቅና የአብሮነትን ለማጽናት የሚያስችል የትስስር ቀናችን አድርጎ መቀበል ይገባል፡፡ ይሄ ስለሰላም፣ ስለአብሮነት የተሻለው መንገድ ነው፡፡ እንዲህ ካልሆነ ለአብሮነታችን አቅም የሚፈጥር ሌላ ነጻ አውጪ ኃይል አናገኝም፡፡ በትላንት ቁርሾ ዛሬን መገፋፋት፣ ለነገ ስቃይ ማስቀመጥ የሚበቃን ጊዜ ላይ ነን፡፡ ስቃይ በሰላም ካልዳነ፣ በቀል በይቅርታ ካልሻረ፣ ጥላቻ በፍቅር ካልታከመ ለሀገራችንም ሆነ ለሌላው ሰጥተን የምንቀበለው አንዳች አይኖረንም፡፡ ጣት በመጠቋቆም ወደነገ ከመሄድ ባለፈ መዳኛ አይሰጠንም፡፡ አንዲት ክፉ ትርክት በጊዜ ካልታከመች እየሰፋችና እየበዛች ከዘመን ዘመን የመሄድ ጉልበት አላት፡፡ ልክ እንደዚህ በጎ ታሪኮችም ጠባሳ ማጥፊያ፣ ሰንበር ማከሚያ ሆነው መጽናናትም መሆን ይችላሉ፡፡

ነገር እያቦካን ብንጋግር ለጥቂቶች ጥጋብ፣ ለብዙሀኑ ደግሞ የሞት ህብስት ነው የሚሆነው። ጥላቻ ጅምላ ጨራሽ መሳሪያ ነው፡፡ በእርቅ ካልሆነ በምንም እንዳይረግብ ሆኖ የተቀመጠ እንጦሮጦስ ነው፡፡ ይሄ እውነታ በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ጥቁር ጠባሳን ከሚተው መጥፎ አጋጣሚዎች ጋር ምስስል ነው፡፡ ማገገሚያችን ውይይትና የጋራ ትርክቶች ናቸው፡፡ ተወያይቶ መግባባት፣ ስለሰላም ዋጋ መክፈል፣ ስለአብሮነት እርባና ያላቸውን ትርክቶች መፍጠር፣ የፖለቲካውን ምህዳር ማስፋት፣ ከአሉባልታና ከትችት ወንበር ስቦ መነጋገር ይሄ ነው እኔ ለሀገሬ ምን አደረኩላት ማለት፡፡

ጨለማው ላይ ብርሀን ሳናበራ ስለጨለማው ብናወራ ምን ይጠቅመናል? እንዴት መጣ? ማን አመጣው? ለምን መጣ? እና ከየት መጣ? የሚሉ መሰረታዊ ጥያቄዎችን ሳንመልስ ወደ መፍትሄው ብናተኩርም ትርጉም የለውም፡፡ አንድ ችግር ከስሩ እንዲነቀል ምንጩ መታወቅ አለበት። ችግሮቻችን እንዲረግቡ ምንጫቸውን ማወቁ ቀዳሚው ርምጃ ነው፡፡ ጨለማችን ላይ ብርሀን የምንረጨው እንዲህ ባለው መንገድ ነው፡፡ ጨለማችን ላይ ብርሀን መዝራት አቅቶን ሁልጊዜ ስለ ጨለማው ብናወራ ትርጉም የለውም፡፡ የሰጥቶ መቀበል ወይም ደግሞ እኔ ለሀገሬ ምን አደረኩ የሚለው ጽንሰ ሀሳብ ነፍስ የሚዘራው ጨለማው ላይ ማተኮራችንን ትተን ጨለማው የሚገረሰስበትን ብርሀናማ የመፍትሄ አማራጭ ስንፈልግ ነው፡፡

እኔ ለሀገሬ ምን አደረኩ? የሚለው ንግግር ዓለም ላይ ከታዩ የለውጥና የተሀድሶ እሳቤዎች ቀዳሚው ነው፡፡ ብዙዎች በዚህ ፍልስፍና በኩል በትውልዱ ላይ ንቃትን በመፍጠር ታሪኮቻቸውን አድሰዋል፡፡ እኛም ከችግሮቻችን ተላቀን ወደፊት እንድንራመድ ከዚህ የተሻለ የንቃትና የብርታት ምንጭ እንደሌለን ስናገር ባለው ዘርፈ ብዙ ፋይዳ ላይ ተመስርቼ ነው፡፡ ለሌላቸው ያለንን በመስጠት ካላቸው የሌለንን መቀበል እንችላለን፡፡

ከሀገር መቀበል ሰጪነት የሌለው ጠባቂነት ነው፡፡ ያልሰጠነውን ለመቀበል መጠበቅ ምን አይነት ስሜት እንዳለው አይጠፋንም፡፡ ይሄ እውነታ አሁን ያለነውን እኛንና ሀገራችንን የሚገልጽ ጥሩ ምሳሌ ነው፡፡ ብዙዎቻችን ያልሰጠነውን የምንጠብቅ ነን፡፡ ሀገሬ ለኔ ምን አደረገችልኝ? በሚል ቅደም ተከተሉን በሳተ መጠየቅ መንግስትን የምንተች፣ ማኅበረሰቡን የምንወቅስ ወቃሾችና ተቺዎች ነን፡፡ ለመቀበል መስጠት ይቀድማል፡፡ ያለንን በጎ ነገር በመስጠት የሌለንን በጎ ነገር ማግኘት ይቻላል መቋጫ ሀሳቤ ነው፡፡

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## ትብብር እና ቅንጅት የሚጠይቀው የሳይበር ደህንነት

ወርቅነሽ ደምሰው

የሳይበር ደህንነት ቀዳሚ የዓለም ስጋት እየሆነ መጥቷል፡፡ የዲጂታል ቴክኖሎጂ መስፋፋትን ተከትሎ ከሚመጣው የሳይበር ደህንነት ስጋት በተጨማሪ የሚፈጠሩት ጥቃቶች በዲጂታል ጉዞ ላይ እንቅፋት መሆናቸው እየተጠቆመ ነው፡፡ ይህን ሁሉ ተከትሎም የሳይበር ጥቃት ተጋላጭነት እየጨመረ መምጣቱ ይነገራል፡፡

የሳይበር ጥቃት ሆነ ተብሎ በኮምፒውተር ሥርዓቶች፣ መሰረተ ልማቶች፣ ኔትዎርኮች ላይ ያልተፈቀዱ አጥፊ ሶፍትዌሮችን በመጠቀም በሕገወጥ መንገድ መረጃዎችን መበዝበዝና አገልግሎት በማስተጓጎል የሚፈጸም ጥቃት ነው፡፡ የሳይበር ደህንነት ስጋት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣቱን ተከትሎ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሳይበር ጥቃቶች የሚያስከትሉት ኪሳራም ተበራክቷል፡፡

መረጃዎች እንደሚያመላክቱት፤ በዓለም አቀፍ ደረጃ እ.ኤ.አ በ2022 ከ5ነጥብ6 እስከ 7 ትሪሊዮን ዶላር፤ በ2023 ስምንት ትሪሊዮን ዶላር በሳይበር ጥቃት የተነሳ ኪሳራዎች ደርሰዋል፡፡ እ.ኤ.አ በ2025 አሥር ትሪሊዮን ዶላር ኪሳራ ሊደርስ ይችላል ተብሎ ተሰግቷል።

የኢንፎርሜሽን ደህንነት መረብ አስተዳደር መረጃዎች እንደሚያመላክቱት፤ በዓለም አቀፍ ደረጃ እየጨመረ የመጣው የሳይበር ጥቃት በኢትዮጵያም በየጊዜው እየጨመረ መጥቷል፡፡ ለዚህም በቅርብ ዓመታት የተደረጉት የሳይበር ጥቃት ሙከራዎችን መመልከት ይቻላል፡፡

በ2008 በጀት ዓመት 214፣ በ2009 በጀት ዓመት 479፣ በ2010 በጀት ዓመት 576 እና በ2011 በጀት ዓመት 791 የሳይበር ጥቃት ሙከራዎች ተደርገዋል፡፡ በ2012 በጀት ዓመት አንድ ሺ075፣ በ2013 በጀት ዓመት ሁለት ሺ 898 እና በ2014 በጀት ዓመት ስምንት ሺ 845 ጥቃት ሙከራዎች ተደርገዋል፤ በ2015 በጀት ዓመት 6ሺ959 የሳይበር ጥቃት ሙከራዎች ተካሂደዋል፡፡ በተለይ ከ2012 ጀምሮ ባሉት በእነዚህ ሦስት ዓመታት የሳይበር ጥቃት ሙከራዎች እየጨመሩ መምጣታቸው መረጃዎቹ ያሳያሉ፡

ኢትዮጵያ ለሳይበር ጥቃት ተጋላጭ እንድትሆን እና ተጋላጭነቱ እንዲጨምር ካደረጉት ምክንያቶች መካከል የሳይበር ምህዳር ተለዋዋጭ በመሆኑ በየጊዜው የሚፈልገውና የሚጠበቀውን አይነት ሆኖ አለመገኘት፣ የአገልግሎቶች ዲጂታላይዝድ መድረግና የአገሪቱ የጂኦፖለቲካ ሁኔታ ተጠቃሽ ናቸው፡፡

የሳይበር ጥቃት መመከት ሳይቻል ቀርቶ ከተከሰተ በአገር ኢኮኖሚ ላይ የሚያስከትለው ውድመት ከፍተኛ በመሆኑ የሚያደርሰው ተጽእኖ ከባድ ነው፡፡ ከዚህ ባሻገር በሀገር ላይ ከፍተኛ ቀውስ ሊያስከትል እንደሚችል መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

የአንድ አገር ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳይ የሚጠበቀው ደህንነቱ የተጠበቀ የሳይበር አገልግሎት ሲኖር ነው። በተለይ ኢትዮጵያ በ2025 ሙሉ ለሙሉ ዲጂታል ኢኮኖሚ ለመተግበር የምታደርገውን ጥረት የሚያግዝ ስርዓት ለመዘርጋት የማይበገር የሳይበር ደህንነት አቅምን መገንባትን ይጠይቃል፡፡

ዲጂታል 2025 ስትራቴጂን ለማሳካት ከተቀመጡ ዋናዋና እቅዶች አንዱ የሳይበር ስነምህዳርን /ኢኮሲስተም/ን በመጠቀም ሲስተሞች ከመዘርጋትና የዲጂታል ኢኮኖሚውን ሊመጥን የሚችል ምህዳር መገንባት ሲቻል መሆኑን የዘርፉ ምሁራን ያመላክታሉ፡፡

> **እንደ አገር ዲጂታል ትራንስፎርሜሽን እየተስፋፋ መሆኑን ተከትሎ እየጨመረ የመጣውን የሳይበር ጥቃት ለመከላከል የሚያስችሉ ሥራዎችን በጋራና በትብብር መስራት ያስፈልጋል፡፡ ዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ስትራቴጂም የሚያስገነዝበውም በትብብር መስራትን ነው፡፡ ዲጂታል ኢኮኖሚው አካታች ሆኖ እንዲሰራ፤ ደህንነቱ የተጠበቀ ሆኖ እንዲሄድ የተማከለ መሆን እንዳለበት ይታመናል**

የአገሪቱን የሳይበር ምህዳር ደህንነት ለማስጠበቅና ሉአላዊነትን ለማስከበር የሳይበር ጥቃቶችን መመከት ኃላፊነት የተሰጠው የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር የሳይበር ደህንነት ለማስጠበቅ የሚያስችሉ በርካታ ሥራዎችን እየሰራ ይገኛል፡፡ አስተዳደሩ ከተለያዩ አጋር አካላት ጋር በመሆን የሳይበር ደህንነትን በማስጠበቅ ረገድ የኅብረተሰቡን ግንዛቤ ለማስፋት የሚያስችሉ ሥራዎች ሲሰራ ቆይቷል፡፡

በቅርቡም የኢንፎርሜሽን ደህንነት መረብ አስተዳደር እና የኢትዮጵያ ሳይበር ደህንነት ማህበር የግሉ ዘርፍና የመንግሥት ተቋማት በተቀናጀ መልኩ የሳይበር ደህንነትን ለማስጠበቅ የሚያስችል ሥራ ለመስራት የሚጠቅም ምክክር አድርገዋል፡፡

ምክክሩ የሳይበር ደህንነትን ከሚመራው የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር፣ ከኢትዮጵያ ሳይበር ደህንነት ማህበር ጋር በመተባበር በሳይበር ደህንነት ዙሪያ ጥናትና ምርምር ከሚሰሩ የተለያዩ ምሁራን ጋር ውይይት ለማድረግ ታልሞ የተዘጋጀ መሆኑን የሚናገሩት የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ዋና ዳይሬክተር ወይዘሮ ትዕግሥት ሃሚድ ናቸው፡፡

እሳቸው እንዳሉት፤ አሁን ላይ የሳይበር ደህንነትን በተመለከተ የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች እየተሰሩ ናቸው። በተለይ በየዓመቱ በጥቅምት ወር የሳይበር ደህንነት የተመለከቱ በርካታ ሥራዎች ይሰራሉ። ይህን ፕሮግራም ለየት እንዲል የሚያደርገው የሳይበር ደህንነት ለማስጠበቅ ከምሁራን፣ ከግልና ከመንግሥት ተቋማት ጋር በተቀናጀ መልኩ መስራት የሚያስችል መሆኑ ነው፡፡

የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ዋና ተልዕኮ ቁልፍ የመንግሥትና የሕዝብ ተቋማትን ደህንነት ማስጠበቅ መሆኑን ያመላክታሉ፡፡ ይህን ተልዕኮ ለማሳካት 24/7 የተሰኘ የሳይበር ኤመርጀንሲና ሪስፖንስ/ድንገተኛ አደጋና ምላሽ/ ቡድን ተቋቁሞ እየሰራ መሆኑን ዋና ዳይሬክተሩ ጠቅሰው፤ ይህም በቁልፍ መሠረተ ልማቶች እና በፋይናንስ ተቋማት ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን ለመከላከል የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን በመታጠቅ የሳይበር ደህንነትን ለማስጠበቅ ዝግጁ ሆኖ ሁልጊዜም በንቃት የሚከታተል ክፍል መሆን ገልጸዋል። በተጨማሪም የፋይናንስ ተቋማት፣ ቁልፍ የመንግሥት ተቋማት እና ግለሰቦች ላይም ጭምር ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን ለመከላከል ብዙ እየተሰራ እንደሆነ አመላክተዋል፡፡

እንደ አገር ዲጂታል ትራንስፎርሜሽን እየተስፋፋ መሆኑን ተከትሎ እየጨመረ የመጣውን የሳይበር ጥቃት ለመከላከል የሚያስችሉ ሥራዎችን በጋራና በትብብር መስራት ያስፈልጋል የሚሉት ዋና ዳይሬክተሯ፤ «ዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ስትራቴጂም የሚያስገነዝበውም በትብብር መስራትን ነው፡፡ ዲጂታል ኢኮኖሚው አካታች ሆኖ እንዲሰራ፤ ደህንነቱ የተጠበቀ ሆኖ እንዲሄድ የተማከለ መሆን እንዳለበት ይታመናል፡፡ ለዚህ የተለያዩ መሠረተ ልማቶችን በጋራ የመጠቀም፣ አገልግሎቶችን ክላውድ ማድረግ ያስፈልጋል» ይላሉ፡፡

መሠረተ ልማቶችን በጋራ ለመጠቀም፣ አገልግሎቶችን ክላውድ ለማድረግም ያስችል ዘንድ ኢትዮ ቴሌኮም፣ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር፣ ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር እና አርተፊሻል ኢንተለጀስ ኢንስቲትዩት በጋራ አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ በጠቅላይ ሚኒስቴር ጽሕፈት ቤት የሚመራ ግብረ ኃይል ተቋቁሞ እየተሰራ መሆኑን ዋና ዳይሬክተሯ አስታውቀዋል፡፡ የሳይበር ደህንነትን ማስጠበቅ ስራ ጥቃቶች ሳይደርሱ በመመከት በአገር ላይ የሚያደርሰውን ተጽዕኖ ከመቀነስ አንጻር ከፍተኛ ሚና እንዳለው ያስረዳሉ፡፡

እንደ ዋና ዳይሬክተሯ ማብራሪያ፤ በኢትዮጵያ የሳይበር ጥቃት እየጨመረ ነው። በተያዘው በጀት ዓመት በስድስት ወራት ውስጥ 4ሺህ 363 የሳይበር ጥቃቶች ደርሰዋል። እነዚህ የሳይበር ጥቃቶች በአይነታቸው የተለያዩ ሲሆኑ፣ የኢሜልና የፊሺንግ ጥቃቶች ተከስተዋል፤ አብዛኛዎቹ ደግሞ የዳታ ስርቆት ጥቃቶች ናቸው፡፡

በአገሪቱ ላይ በተቃጡት የሳይበር ጥቃቶች በአብዛኛው ተጠቂ እየሆኑ ያሉት የሚዲያና የፋይናንስ ተቋማት ናቸው፤ እስካሁን የተሰነዘሩት ጥቃቶች መሠረታዊ የሚባሉት መሠረተ ልማቶች ማቋረጥ ላይ አልደረሱም፡፡ እነዚህ ጥቃቶች የተለያዩ ቢሆኑም፣ አብዛኛውን ጊዜ በንቃተ ህሊና እጥረት የሚመጡ ናቸው፡፡

ተቋሙ የሳይበር ደህንነትን በተመለከተ ግንዛቤ በመስጠት እና ተቋማት እንዲጠነቀቁ በማድረግ የሳይበር ጥቃቶችን ለመከላከል ጥረት እያደረገ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡ የሳይበር ደህንነት ሁሉንም ሰው የሚመለከት ጉዳይ መሆኑን ጠቅሰው፣ ግንዛቤን በማስፋት መከላከል ተገቢ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የኢትዮጵያ ሳይበር ደህንነት ማህበር ፕሬዚዳንት ብርሃኑ በየነ (ዶክተር) በበኩላቸው፤ ማህበሩም የሳይበር ደህንነት እንደሚመለከተው ጠቅሰው፣ መቋቋሙ እጅግ አስፈላጊነት መሆኑን ተናግረዋል፡፡ የተቋቋመበት ዓላማ በሳይበር ደህንነትና በዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ዘርፍ ያሉ ባለሙያዎች ከአገር ውስጥ ከውጭም በማሰባሰብ የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን እንዲያግዙ የሚያደርግ ፕላትፎርም እንዲኖር ለማድረግ ያለመ ነው ብለዋል፡፡

ማህበሩ አሁን ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት፣ በሳይበር ደህንነትና በዲጂታል ትራንስፎርሜሽን የግንዛቤ ተሳትፎ እንዲኖራቸው እየሰራ መሆኑን ጠቅሰው፤ በተለይ ወደ ዲጂታል ትራንስፎርሜሽን የገቡት የፋይናንስ፣ የኢንሹራንስ እና የመንግሥት የተለያዩ ድርጅ ቶችን አንድ ላይ በማሰባሰብ በሚቀጥሉት ጊዜያት በኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽንና ቴክኖ ሎጂ ፕሮጀክት ውስጥ የሳይበር ደህንነት የማኔጅንመንት ጉዳይ ተቀናጅቶ ለመስራት የሚያስችል አሠራር እንዲኖር እየሰራ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

እሳቸው እንዳስታወቁት፤ ማህበሩ ቀደም ሲል የተለያዩ የምክክር መድረኮችን አዘጋጅቶ ነበር፤ አገር አቀፍ የኢስትሪንግ ኮሚቴ ተቋቁሞ በሳይበር ደህንነት ዙሪያ የተለያዩ ድርጅቶች (ኢትዮ ቴሌኮሙኒኬሽን፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድ እና የገንዘብ ሚኒስቴር፣ ገቢዎች ሚኒስቴር እና ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር እና ሌሎችም ተቋማት) የተካተቱበት ምክክር ተካሄዷል፡፡ የጥናትና ምርምር ሥራዎች በተጠናከረ መንገድ እንዲካሄዱና እንዲታተሙ ምክክር ከተደረገ በኋላ ጥሩ ውጤት ተገኝቷል፡፡

እንዲህ አይነት የምክክር መድረኮች ማጠናከር እንደሚገባ ጠቅሰው፣ ይህን በማጠናከር የሳይበር ደህንነትን አስመልክቶ በተለይ ጥናት ላይ የተመሰረቱ ሥራዎች እንዲሰሩ ይደረጋል ብለዋል፡፡ ይህም መድረክ ከሁሉም ዘርፍ የተውጣጡ ባለድርሻ አካላት የተገኙበት መሆኑን ጠቅሰው፣ ጥሩ ውጤት እንደሚገኝበት እምነታቸው መሆኑን ተናግረዋል።

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር ዴኤታ ይሽሩን ዓለማየሁ (ዶክተር) ሀገሪቱ ዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ስትራቴጂን ለማስተግበር ከጀመረቻቸው አራት መሰረታዊ ጉዳዮች መካከል የመጀመሪያው የዲጂታል መሠረተ ልማት አስቻይ ሥርዓቶችን መዘርጋት መሆኑን ጠቅሰው፤ በዚህ ውስጥ በዋናነት የሚታየው የሳይበር ደህንነት ፕላትፎርም መሆኑን አመላክተዋል፡፡

የሳይበር ምህዳር ደህንነት የመጠበቅ ጉዳይ ለማንም የሚተው ሳይሆን ከሁላችንም የሚጠበቅ ነው ሲሉ ሚኒስትር ዴኤታው አስገንዝበዋል፡፡ የዲጂታል መሠረተ ልማት አስቻይ ሥርዓቶችን በመዘርጋት ሂደት የሳይበር ደህንነት ምህዳሩን ለመጠቀም አሁን አገልግሎት እየተሰጡ ያሉት እንደ ዲጂታል መታወቂያ እና ዲጂታል የክፍያ ሥርዓት አይነት ፕላት ፎርሞች የሳይበር ምህዳሩን መጠበቅ ካልተቻለ አደጋ ላይ ይወድቃሉ።

እሳቸው እንዳብራሩት፤ ሌላው ኢ ገቨርንመንት፣ ኢ ሰርቪስ እና ኢ ኮሜርስን የመሳሰሉት የዲጂታል ፕላትፎርሞች የሳይበር ምህዳሩ ጤናማ ካልሆነና ችግር ካለበት ደህንነታቸው በሚገባ ተጠብቆ ታአማኒ በሆነ መንገድ ሊካሄዱ አይችሉም፡፡ የሳይበር ደህንነት መጠበቅ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ከዚህም አንጻር እያንዳንዱ በመንግሥት፣ በግሉ ዘርፍ፣ በማህበራት በምርምር ተቋማት እና፣ በተለያዩ ኢንዱስትሪዎች የሚሰሩ ሥራዎች ተደምረው እንደ አገር ትልቅ አቅም ይፈጥራሉ፡፡

በኢንስቲትዩቱ መገንባትና አቅም በመፍጠር ረገድ በኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳዳር የሚሰሩ ብዙ ሥራዎች መኖራቸውን ጠቅሰውም፤ የዲጂታል ዘርፉን የሚመራው የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ሁሉን አቀፍ ድጋፍ በሚባል ደረጃ ሁሉንም ዘርፍ በመደገፍ እንደ አገር በዲጂታል፣ በሳይበር፣ በአይሲቲ እና በሰው ሠራሽ አስተውሎት ቴክኖሎጂ ላይ ድጋፍ ለማድረግ ይሰራል ብለዋል።

# ወቅታዊ ትንታኔ

# የባሕርበር የማግኘት ዲፕሎማሲያዊ ጥረቶችና እያስገኙት ያለው ውጤት

ስምስም መንግሥቱ

ኢትዮጵያ ትገለገልባቸው የነበሯትን ምጽዋና አሰብ ወደቦችዋን ካጣች ጊዜ ጀምሮ የባሕር በር አልባ ከሆነችም ዓመታት ተቆጥረዋል:: አሁን ደግሞ በሰለጠነ ዲፕሎማሲና በሰጥቶ መቀበል መርህ በሊዝ የወደብ ባለቤት ለመሆን የሚያስችላትን ከሶማሊ ላንድ ጋር የመግባቢያ ሰነድ መፈራረሟ ይታወሳል::

በኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ እና በሶማሊ ላንድ ፕሬዚደንት ሙሴ ባሂ መካከል ከሶስት ወራት በፊት የተደረገው ስምምነት ኢትዮጵያ የባሕር በር ለማግኘትና ለማልማት የሚያስችል ነው:: ይሄን ተከትሎ ኢትዮጵያ ትክክለኛ የሆነ እርምጃ መውሰዷንና መብቷም እንደሆነ ብዙዎች የድጋፍ ሀሳብ ሰጥተዋል::

በአንፃሩ ደግሞ ስምምነቱ ከተፈፀመበት ጊዜ ጀምሮ ሶማሊ ላንድ በዓለም እውቅና የተሰጣት ሉዓላዊ ሀገር እንዳልሆነችና የወደብ አማራጭ መሆን እንደሌለባት በመንቀፍ፣ ስምምነቱ ወደ ተግባር እንዳይለወጥ የተለያዩ ኃይሎች ተንቀሳቅሰዋል። በተለይም ጉዳዩ በቀጥታ የማይመለከታቸው ሀገራት ጉዳዩን ለማራገብ ሲሞክሩ ቆይተዋል::

ኢትዮጵያ አበጀሽ ብለው የደገፏት አቅም ሆነዋት፤ ለነቀፏትም ጆሮ ሳትሰጥ በአቋሟ ፀንታ የባሕርበር ባለቤት የምትሆንበትን አማራጮች ከመፈለግ ወደኋላ አላለችም:: ይሄ ቁርጠኝነት በምን መልኩ መቀጠል አለበት? ከማኅበረሰቡስ ምን ይጠበቃል? ለሚለው በኢፌዴሪ የሕገመንግሥት አጣሪ ጉባኤ ከፍተኛ የሕገመንግሥት ተመራማሪ አቶ ዓምደገብርኤል አድማሱ አነጋግረን የሚከተለውን ሀሳብ ሰጥውናል::

እርሳቸው እንደሚሉት በኢትዮጵያ እና በሶማሊ ላንድ መካከል ስምምነት ላይ የተደረሰው የባህር በር የማግኘት ጉዳይ ወደ ተግባራዊ ሂደት እንዲሸጋገር፤ ዲፕሎማሲው ተጠናክሮ መቀጠል አለበት::

እንደ አቶ ዓምደገብርኤል ማብራሪያ፤ ኢትዮጵያ በዓለም ከሌሎች የአፍሪካ ሀገራት ተደማጭነት ያላት፣ በዲፕሎማሲ እንቅስቃሴዋም ጫና መፍጠር የምትችል ሀገር ናት:: የተባበሩት ምንግሥታት ድርጅት ከመመስረቱ በፊት አፍሪካን ወክላ ሊግኦፍኔሽን ላይ በመሳተፍ የአፍሪካን መብት ያስከበረች፣ ለአፍሪካ ድምጽ መሆን የቻለች ሀገር ናት::

የአፍሪካ ሕብረት መቀመጫም በመሆኗ ከሌሎቹ የአፍሪካ ሀገራት በተሻለ ታላቅ ስም አላት:: እነዚህ ሁሉ በዲፕሎማሲው ተጽእኖ እንድትፈጥር ያስችሏታል::

ተቀባይነቷን በመጠቀም በዲፕሎማሲው የምታደርገው እንቅስቃሴ እየተቃወሟት ያሉ ሀገራትንም ሆኑ ግለሰቦችን ማሳመንና ከድርጊታቸውም እንዲቆጠቡ ማድረግ ትችላለች። በተጨማሪም የባሕር በር ለማግኘት ከሶማሊ ላንድ ጋር በፊርማ ያደረገችው የውል ስምምነት ወደ ተግባር እንዲቀየር ያስችላታል:: በመሆኑም በዲፕሎማሲ መግፋትና መበርታት የተሻለ ነው::

አካባቢ ላይ ሁከት፣ ትርምስና ግጭት ለማስነሳት የሚንቀሳቀሱ አካላት ትክክል እንዳልሆኑ ለማሳየት እንዲሁም ከሶማሊ ላንድ ጋር የተደረገው ስምምነት ሕጋዊነትና ጠቀሜታውን በተመለከተ ሌላው ዓለም እንዲያውቀው በማድረግና መረጃም በመስጠት ተከታታይነት ያለው የዲፕሎማሲ ሥራ ያስፈልጋል::

መታወቅ ያለበት ነገር ኢትዮጵያ እያደረገች ያለው ሕጋዊና በዓለምአቀፍም ተቀባይነት ያለው ነው:: ተጠቃሚ ለመሆን የወሰደችው አማራጭም በኃይል ሳይሆን፣ በሰጥቶ መቀበልና በስምምነት ላይ የተመሰረተ ነው:: በመሆኑም ይህ ፍላጎትዋ እንዲሳካ፣ ዓለምአቀፍ እውቅና እንዲያገኝ እንዲሁም ተቀባይነቱ ሥር እንዲሰድ ጠንካራ የሆነ የዲፕሎማሲ ሥራ መሥራት ይጠበቅባታል::

መንግሥት የጀመረውን የባሕር በር የማግኘት ጥረት ከዳር ለማድረስ ሕዝቡን የበለጠ ማሳተፍ እንደሚገባም አቶ ዓምደገብርኤል ይመክራሉ:: ይህ ሲሆን መንግሥትንና ሕዝብን መነጣጠል እንደማይቻልና ጉዳዩ የአንድ አካል ሳይሆን፣ የጋራ እንደሆነ ማሳየት ያስችላል ይላሉ::

እርሳቸው እንዳሉት በሕዝብና በሕዝብ መካከል ወይንም በመንግሥትና በሕዝብ መካከል የሚያነጋግሩ፣ የሚያከራክሩና የሚያጨቃጭቁ ነገሮች ቢኖሩም፤ የባሕር በር የማግኘት ጉዳይ ግን የጋራ ጉዳይ ነው::

እንደ ሀገርም ታሪክ የሚሰራበትና ለሚመጣውም ትውልድ የሚቆይ ታሪክ በመሆኑ ጉዳዩ የአንድ ወገን ብቻ መሆን የለበትም:: ኢትዮጵያ ከዛሬ 40 ዓመት በፊት አንድ ወደብ ብቻ ሳይሆን ወደቦች የነበራት ሀገር ናት:: በሂደት በታሪክ አጋጣሚዎች ነው ወደብ አልባ ለመሆን የቻለችው::

የኢትዮጵያን የቀድሞ ገናናነቷንና ከፍ ያለውን ታሪኳን ወደነበረበት መመለስ የዜጎችዋ ድርሻ ስለሆነ በተለያየ መንገድ ማገዝና መደገፍን ይጠይቃል:: መደበኛ የሆኑ የመገናኛ ብዙሃንና ማኅበራዊ ድረገጾችን (ሶሻል ሚዲያ) የመገናኛ ዘዴዎች አማራጮች ማድረግ ይቻላል::

ኢትዮጵያ በውስጥ የገጠማት አለመረጋጋትና የሰላም ሁኔታ የባሕርበር ለማግኘት በኢትዮጵያና በሶማሊ ላንድ መካከል የተደረገው ስምምነት ላይ ሊኖረው ስለሚችለው ተጽእኖ በአንዳንዶች የሚነሳውንም ስጋት አቶ ዓምደገብርኤል አንስተዋል::

እንደርሳቸው ማብራሪያ የባሕር በር ስምምነቱ ከታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ፕሮጀክት ቀጥሎ እንደ አንድ ሀገራዊ ፕሮጀክት ማየት ይቻላል:: የባሕርበር ማግኘት ትልቅ ጉዳይ ነው:: ኢትዮጵያ አሁን እጅግ ከፍተኛ የሆነ ክፍያ በመፈጸም ነው የጅቡቲ ወደብን እየተጠቀመች ያለችው::

የራሷን ወደብ ቢኖራት ግን ወጪን ይቀንስላታል:: ታወጣ የነበረውን ገንዘብም ሀገርንና ሕዝብን የሚጠቅም የልማት ሥራ ላይ ታውላለች:: የባሕር በር ጉዳይ የሉአላዊነት ነጻነትም ጉዳይ ነው:: የበለፀጉት እንደነቻይና፣ አሜሪካን፣ ጣሊያን፣ ፈረንሳይ የመሳሰሉት ሀገራት ለራሳቸው ልእልና ማሳያ ጅቡቲ ላይ የባሕር በር ቦታ ላይ መሬት የገዙበት አጋጣሚ መኖሩ አይዘነጋም::

ለዚህ ነው የባሕርበር ጉዳይ እንደዋዛ መታየት የሌለበት። በሀገር ውስጥ ያለው አለመረጋጋትና የሰላም ጉዳይ ወደብ የማግኘት ጥያቄ ላይ ተጽእኖ ማሳደር የለበትም:: የኢትዮጵያን እድገት ለማይፈልጉ መንገድ መክፈት አያስፈልግም:: የውስጥ አለመረጋጋቱ የኢትዮጵያን እድገት በማይፈልጉ አካላት ተገቢውን እውቅና እንዳያገኝ ማድረግና ጉዳዩንም ሁሉም ቆም ብሎ ማሰብ ያስፈልጋል ብለዋል::

እንደ አቶ ዓምደገብርኤል ማብራሪያ፤ ውል በተዋዋዮች መካከል ሕግ ነው:: በሀገራት መካከል የሚደረግ የሁለትዮሽ ስምምነት ደግሞ ሌሎች ዓለምአቀፍ ሕግጋቶችና ስምምነቶች የማይጣረስ ከሆነ እንደሕግ ነው የሚቆጠረው::

ስለዚህ ኢትዮጵያ የወደብ አገልግሎት ለማግኘት ከሶማሊ ላንድ ጋር ያደረገችው ስምምነት ሰጥቶ መቀበልን መርህ የተከተለ ነው::

ኢትዮጵያም ሆነች ሶማሊ ላንድ የሄዱበት መንገድ ሕገወጥ ቢሆን ኖሮ፣ የዓለምአቀፍ ሕግጋትንም የሚጥስ ቢሆን ኢትዮጵያ ላይ ከፍተኛ ጫና ይፈጠርባት ነበር:: ኢትዮጵያ የፈፀመችውን የውል ስምምነት ከግብጽና ሶማሊ ሪፐብሊክ በስተቀር በተባበሩት መንግሥታት ዓለምአቀፍ ድርጅቶችም ይሁን በአፍሪካ በቀጠናው ትክክል አይደለም ወይንም ሕገወጥ ነው በሚል እስካሁን የቀረበ ነገር የለም::

ግብጽ፤ ከታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ግንባታ ጋር በተያያዘ አካላት ታሪካዊ ጠላትነት ስምምነቱን ተቃውማለች። ግብጽ በቀጠናው ላይ ትርምስ ለመፍጠር ማንኛውንም አይነት መስዋእትነት ለመክፈል ዝግጁ መሆኗን በግልጽ አሳውቃለች።

ሶማሊም የሶማሊ ላንድ ግዛት የኔ ነው፤ የኔን ሉዓላዊነት መድፈር ነው በሚል በተመሳሳይ በኢትዮጵያና በሶማሊ ላንድ መካከል የተደረገውን ስምምነት አልተቀበለችውም:: የሶማሊው ፕሬዚደንትም ስምምነቱ ሉዓላዊነታቸውን የሚነካ መሆኑን ሲጠቅሱ ይሰማሉ:: አሁን ባለው ሁኔታ ስምምነቱን በጥሩ መልክ ለመቀበል ፈቃደኛ ሆነው ያልተገኙት፣ በቀጠናው ብጥብጥ እንዲነሳና ጉዳዩም እንዳይሳካ እያደረጉ ያሉት እነዚህ ሁለቱ ሀገራት ናቸው::

ግብጽም ሆነች ሶማሊያ ስምምነቱ ትክክል እንደሆነ ሳይገነዘቡት ቀርተው ሳይሆን፤ ከኢትዮጵያ ጋር ባላቸው ታሪካዊ ጠላትነት የተነሳ ነው:: ሁለቱ ሀገራት በዚህ መልኩ መንቀሳቀሳቸው ስምምነቱ በሚፈለገው ፍጥነት እንዳይሄድ ሊያደርግ እንደሚችልም አቶ ዓምደገብርኤል ገልጸዋል::

ሆኖም ኢትዮጵያውያን የያዙት ሀሳብ ትክክል ስለሆነ የባሕር በር የማግኘት ጥረታቸውን አጠናክረው መቀጠላቸው የማይቀር መሆኑን አስረድተዋል::

የሁለቱ ሀገራት አካሄድ በቀጠናው ግጭት እንዲስፋፋ ሊያደርግ ይችላል የሚለውን ስጋት በተመለከተ አቶ ዓምደገብርኤል ሲናገሩ፤ «በስምምነቱ ውስጥ ኃይል የሚባል ነገር የለም፤ ኢትዮጵያና ሶማሊ ላንድ በግዴታ ሳይሆን፣ በስምምነት የፈጸሙት ጉዳይ ነው:: ሁለቱ ያደረጉት ስምምነት ለጦርነት የሚያነሳሳ ባለመሆኑ ኃይል ወደመጠቀም የሚያደርስ ነገር የለም::» ብለዋል

አቶ አምደ ሚካኤል አክለው እንደሚገልጹት በዚህ ስምምነት ውስጥ ደግሞ ማንም ከልካይ አካል የለም:: ሊኖርም አይችልም:: ግብጽና ሶማሊያም ቢሆኑ መከልከል አይችሉም:: እናም መከልከል የማይችሉት ነገር ላይ ግችትና ሁከት ቢፈጥሩ ችግሩ መልሶ ለእነሱ እንደሚተርፍ አስረድተዋል::

በአሁኑ ጊዜ የባሕርበር ማጣት ማለት በቅኝ መገዛት ማለት ነው የሚሉት አቶ ዓምደገብርኤል፤ የባሕር በር የሌላቸው ሀገራት በጣም ጥቂት ሲሆኑ፣ እነርሱም በሕዝብ ብዛታቸውና በቆዳ ስፋታቸው ትንሽ የሚባሉ ናቸው::

ኢትዮጵያ ግን ከአንድ መቶ ሚሊዮን ሕዝብ በላይ ያላት ሀገር ናት:: የባሕር በር አልባ መሆን አይገባትም:: የኢኮኖሚ የእድገት እንቅስቃሴን ወደኋላ የሚጎትትና በተለያየ መልኩ ጉዳት የሚያስከትል በመሆኑ የባሕር በር መኖሩ ግዴታ ነው ሲሉ ሃሳባቸውን ቋጭተዋል::

የአፋር ክልል ፕሬዚደንት አማካሪ አቶ አህመድ ያሲን ሊሊሳ በበኩላቸው፤ በኢትዮጵያ በኩል የተጀመረው የወደብ ባለቤት የመሆን ጥያቄ መቀጠል አለበት ይላሉ:: ለዚህ ቁልፉ መሳሪያ ደግሞ ዲፕሎማሲ መሆኑን አስምረውበታል። «ሰላማዊ ድርድር ዘለቄታዊ መፍትሄ ያስገኛል:: የኃይል አማራጭ ግን ዓላማን ያሰናክላል:: እቅድንም ወደኋላ ይጎትታል:: ከጥፋት በስተቀር ውጤት ላይ አያደርስም:: ለዚህ ነው ኃይልን በአማራጭነት መውሰድ የማይመከረው» ሲሉም በዲፕሎማሲ መጠንከሩ የተሻለ እንደሆነ አስረድተዋል::

ዜጋውም መንግሥት ለሚጠይቀው ድጋፍ ተባባሪ ሆኖ ለመገኘት ዝግጁ መሆን አለበት ይላሉ:: መንግሥት እንዲበረታታ፣ የባሕር በር ለማግኘት የተፈፀመው የውል ስምምነት ፊርማ ወደ ተግባር እንዲለውጥ የሕዝብ ድጋፍ ያስፈልጋል ብለዋል::

በአፋር በኩል መንግሥት የጀመረውን ከዳር እንዲያደርስ ለማገዝ ዝግጁ እንደሆነም ተናግረዋል:: በመንግሥት የተጀመረው እውን ሆኖ ለማየትና ኢትዮጵያ የባሕርበር እንዳታጣ የአፋር ሕዝብ ቀድሞውኑ ያሰማ የነበረው ጩኸትም መልስ እንደሚያገኝ ተስፋ አድርገዋል:: ከአሰብ ባሕር ውስጥ የሚጠመድ አሣ እንደናፈቃቸውም ገልጸዋል::

አቶ አሕመድ ታሪክንም ወደኋላ መለስ አድርገው እንዳስታወሱት፤ ኢትዮጵያን የባሕር በር ያሳጣት የቀኝ ግዛት አባዜ ያለባቸው ለሀገር ጥቅም የማያስቡ ናቸው ይላሉ:: ሪፈረንደም በሚል ሰበብ የተፈፀመው መለያየት የፈጠረው ጠንቅ ነው ሲሉም ይገልጻሉ::

እርሳቸው እንዳሉት በወቅቱ ሕዝብ የሚሰማው አጥቶ እንጂ ሪፈረንደም ሊያስከትል የሚችለውን መዘዝ አስመልክቶ ተቃውሞውን አሰምቷል:: እስካሁንም የቀይ ባሕር አፋሮች በተለያየ መንገድ ከመታገል ወደኋላ አላሉም:: አፋርን ሲያስተዳድሩ የነበሩት ሱልጣን አሊሚራ ሀንፍሬ ቀይ ባሕር የአፋር እንደሆነ ጭምር በመናገር ኢትዮጵያ ወደብ አልባ እንዳትሆን ብዙ ታግለዋል::

«በአፋር ባሕል ድንበር የለም:: የአፋር ልጅ ወይ አባቱ ወይንም እናቱ፣ ወገኑ በጅቡቲ፣ በኤርትራ ስለሚኖር በመካከላችን ልዩነት አለ ብሎ አያምንም» ሲሉም ያስረዳሉ። የክልሉ መሪ ያደረጉት ትግልም ሆነ የህሕቡ ጩኸት መቀማቱን ነው አቶ አሕመድ የገለጹት::

ያን ጊዜ ሕዝብ ያሰማው የነበረው ጩኸት ትክክል እንደሆነና በወቅቱ ጩኸቱ ባለመሰማቱ ኢትዮጵያን ዋጋ እንዳስከፈላት እማኝ መጥራት አያስፈልግም ያሉት አቶ አሕመድ፤ የባሕር በር አለመኖሩ እያስከተለ ያለው ችግር እየታየ መሆኑን ነው ያስረዱት::

ለወደብ ኪራይ የምታወጣው ወጪ የኢኮኖሚ አቅሟን እየተፈታተነ እንደሆነ ጠቅሰዋል:: ኢትዮጵያን የሚያክል ሀገር የባሕር በር አልባ መሆን ቁጭት ውስጥ የከተተው ሕዝቧን ብቻ ሳይሆን፤ ወዳጆችዋ የሆኑትን የዓለም ሀገራት ጭምር እንደሆነም አመልክተዋል::

ያለፉ መሪዎች ኢትዮጵያ ትገለገልባቸው የነበሩ የባሕርበሮችዋን አስጠብቃ እንድትቆይ ከማድረግ ይልቅ፤ አሳልፈው ለሌላ መስጠታቸው ታሪካዊ ስህተት እንደሆነ የሚገልጹት አቶ አሕመድ፤ የባለቤትነት መብቷ እንዲረጋገጥላትና ከሶማሊ ላንድ ጋር ያደረገችው ስምምነት ተግባራዊ ሆኖ ተጠቃሚ ለመሆን እያደረገች ያለው እንቅስቃሴ የሚበረታታ ነው ይላሉ::

የሕገመንግሥት ተመራማሪው አቶ ዓምደገብርኤልም ሆኑ የአፋር ክልል ፕሬዚደንት አማካሪ አቶ አሕመድ ስምምነቱን ተፈፃሚ ማድረግ የሚቻለው ዲፕሎማሲውን በማጠናከር እንደሆነ አስምረውበታል::



አቶ ዓምደገብርኤል አድማሱ ፣



አቶ አህመድ ያሲን ሲሲሳ፣

ማህበራዊ

# ሴቶች

## በ «አራስ ቤት» የታበሱ እንባዎች

እየሩስ ተስፋዬ



የባሌ ጎባ ልጅ ነች፡፡ ያለ አባት የምታሳድገውን የአራት ዓመት ልጇን ለመርዳት ወደ አዲስ አበባ ከመጣች ሦስት ዓመታትን አስቆጥራለች፡፡ እናት፣ አባት፣ እህት እና ወንድም የላትም፡፡ ብቸኛዋ እናት ሠላም ጌታቸው ትባላለች (ስሟ የተቀየረ)፡፡ ልጇን ለአክስቷ ሰጥታ ነው ወደ አዲስ አበባ የመጣችው፡፡ በአንድ ሆቴል ጽዳት መሥራት ጀመረች፡፡ በሆቴሉ ምንም የሚቸግራት ነገር የለም፡፡ የሚሰጣት የወር ደመወዝ በየወሩ ለልጇ ትልካለች፡፡ በሂደት ወደ ሆቴሉ ጎኑን ለማሳረፍ ከሚመጣ ሰው ጋር ተዋወቀች፡፡ ትውውቃቸው አድጎ በፍቅር ለሁለት ዓመት ያህል ቆዩ፡፡

ይህ ሰው ለሠላም በጣም ጥሩ የሚባል ዓይነት ሰው ነበር፡፡ «አይዞሽ!» ይላታል፡፡ ልጇን እንድታሳድግ ያበረታታል፡፡ ሠላም በጥቂቱም ቢሆን አይዞሽ የሚል ሰው በማግኘቷ ልቧ ያረፈ ይመስላል። ሰውነቷም ጨመርመር አለ፡፡ ነገር ግን የእርሷ መወፈር በተለየ መንገድ የታያት ጓደኛዋ «ምንድ ነው በጣም እየወፈርሽ እኮ ነው? የተፈጠረ ነገር አለ እንዴ?» ብላ ብትጠይቃት ምንም የተፈጠረ ነገር እንደሌለ በልበ ሙሉነት መለሰችላት፡፡ መልሷ ያልተዋጠላት ጓደኛዋ ግን ወደ ሕክምና ተቋም ሄዳ ምርምራ እንድታደርግ አሳሰበቻት፡፡

ሠላም ሃሳብ ያዛት፡፡ ወደ ሕክምና ተቋም አቀናች። ስትመረመር ለእርሷ መርዶ የሆነ ነገር ተነገራት። ነፍሰጡር ናት፡፡ ለሁለት ዓመት በፍቅር ቆይተናል ላለችው ሰው ነገረችው፡፡ እርሱም «ታዲያ ምን ችግር አለው? እናሳድገዋለና» አላት፡፡ በፍጥነት ክትትሏን እንድትጀምር ነገራት፡፡

እናት ለልጇ ያላትን ሁሉ ብር ስለምትልክ እጇ ላይ ምንም አይኖራትም፡፡ «በዚህ ብር ተመርመሪ» ብሎ በሰጣት ብር አልትራሳውንድ ታየች፡፡ እርግዝናዋን ብታውቀውም ያላሰበችው ሆነ- መንታ መጸነሷ ተነገራት። ተደናገጠች፡፡ የምትሆነው ጠፋት፡፡ ዶክተሩ ዕድለኛ መሆኗን ቢነግራትም እርሷ ግን መውለድ እንደማትፈልግ ነገረችው። አሁን ምንም ማድረግ እንደማትችል እና ጊዜው እንዳለፈ ቢነግራትም ማሳቧን አላቆመችም ነበር፡፡ በተደጋጋሚ «መንታ መሆኑን ሲያውቅ ቢከደኝስ?» ብላ ፈራ ተባ እያለች ነገረችው፡፡ «ያስብልኛል፡፡ ይረዳኛል» ያለችው ፍቅረኛዋ ይህንን ከሰማ በኋላ እንደፈራችው ጥሏት ጠፋ፡፡ «አለ» የተባለበት ቦታ ሁሉ ቢፈልግ ዱካውን ማግኘት አልተቻለም፡፡

አማራጭ አልነበራትምና ሥራዋን ቀጠለች፡፡ በሥራ ቦታዋ ሰዎች እግርዝናዋን በተለይም አለቃዋ እንዳታውቅባት ጥንቃቄ ታደርግ ነበር፡፡ አንድ ቀን ሥራዋን ጨርሳ ባለችበት ወቅት ድንገት ንፋሱ ልብሷን አነሳው፡፡ ሆዷን የተመለከተችው አሰሪም ተጠራጥራ ጠየቀቻት፡፡ እርሷም የተፈጠረውን ነገር በዝርዝር ተናዘዘች፡፡ ግራ የተጋባችው አሰሪዋ «በቃ ልጁን አዝለሽም ቢሆን ሥራሽን ትሠሪያለሽ፡፡ »ብላ ብትነግራትም መንታ መጸነሷን ስትነግራት ምን መመለስ እንዳለባት ግራ ተጋባች፡፡

አሠሪዋ አንድ ሃሳብ አመጣች «ልጆቹ ከተወለዱ በኋላ ለምን ለመንግሥት አንሰጥም ?» አለቻት ሠላምም በዚህ ሃሳብ ተስማማች፡፡ አለቃዋ ድጋሚ ሌላ ሀሳብ አመጣች። ልጆቹ ከተወለደ በኋላ የሚወስዱ ሰዎች መገኘታቸውን ነገረቻት፡፡ ልጆቹን ለመውሰድ አንዲት ሴት ከአለቃዋ ጋር ብዙ ንግሮችን ታደርጋለች፡፡ ሠላምን ግን አንድም ቀን አውርታት አታውቅም፡፡ ሁለቱ የማይተዋወቁ ሰዎች ስምምነት አደረጉ፡፡ ሠላም ልጆቿን ስለምትወስድላት ሴት ምንም መረጃ እንዳይኖራት እና ልጆቹም ከተወለዱ በኋላ ማን እንደሚወስዳቸው ዝርዝር መረጃ መጠየቅ እንደሌለባት ጭምር ተስማሙ፡፡

ሠላም «ልጆቼን ይገዬ ጎዳና ከምወጣ ብትወስዳቸው ይሻላል» ብላ የወለደች ቀን ልጆቿን ልትሰጥ ቃል ተግባቡ። የማይደርስ የለምና ሠላም ለወሊድ ወደ ዘውዲቱ ሆስፒታል ሄደች፡፡ ወንድ እና ሴት ልጆችን በሠላም ተገላገለች፡፡ ልጆቿን ለማታውቃት ሴት ለመስጠት ፈራ ተባ እያለች የአሰሪዋን የቅርብ ሰው መጠባበቅ ጀመረች፡፡

ሠላምን የስድስት ወር ነፍሰ ጡር ከሆነችበት ጀምሮ እስከትወልድ ድረስ የምትከታተላት ሴት ሃሳቧን ቀየረች። ልጆቹን እንደማትወስዳቸው አስረግጣ ተናገረች፡፡ ይህ ዜና ለሠላም እና ለአሠሪዋ መጥፎ ዜና ነበር፡፡ አራሷ እናት ይህንን ስትሰማ ቀኑ ጨለመባት፡፡ ምን እንደምታደርግ ግራ ገባት። ከወለደች ሰዓት ጀምሮ ሥራዋ ለቅሶ ብቻ ሆነ፡፡ መሄጃ የላትምና ዕድሏን ረገመች፡፡

በዚሁ ሁሉ ሂደት ግን አንዲት ዶክተር የሠላም ሁኔታ ትከታተል ነበርና ወደ መፍትሄው እንዲያመሩ አነጋገረቻት፡፡ እስከ ስድስት ወር የሚያርሳት ድርጅት መኖሩን አበሰረቻት፡፡ የዚህችን ሴት እና የልጆቿን ሕይወት የታደገው በጎ አድራጎት ድርጅት «የአምላክ ልጆች ፋውንዴሽን» ይባላል፡፡

### አዲስ ሕይወት

ሠላም ዛሬ በአራስ ቤት ጥሩ ቆይታ እያደረገች ነው። ልጆቿን እስከ ስድስት ወር ታቆያለች፡፡ እንዲሁም የእጅ ሥራ ስልጠና እየወሰደች ትገኛለች። ሠላም በትናንት ሃሳቧ ትጸጸታለች፡፡ ዛሬ ጠንካራ ሆናለች፡፡ አራት ወራትን በአራስ ቤት በጥሩ ሁኔታ እያሰለፈች ሲሆን፤ በአራስ ቤቱ ያሉ ሁሉ እያደረጉት ስላለው በጎ ነገር ምስጋናዋን ታቀርባለች፡፡ ከአራስ ቤት ወጥታ የተለያዩ የእጅ ሥራዎችን እየሠራች ልጆችን ለማሳደግ አስባለች፡፡

### ደግሞ ሌላ ታሪክ

የአምላክ ፍቅር ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ጀምሮ ከዩኒቨርሲቲ ተመርቆ እስከሚወጣ ድረስ ትምህርቱን የተከታተለው በአሜሪካ ነበር፡፡ ከምርቃቱ በኋላ ሀገሩን የማገልገል ራዕይ ነበረው፡፡ ግን አልሆነም። ሞት ቀደመው፡፡ ከተመረቀ ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ነበር በድንገት ሕይወቱ ያለፈው፡፡ የአምላክ እናት እና አባት ከጎኑ አልነበሩም፡፡ ከተራራቁ ረዥም ጊዜ ነበርና እንደተነፋፈቁ እስከወዲያኛው ተለያዩ፡፡ ያጡት የበኩር ልጃቸውን ነበርና ሀዘናቸው እጅግ በረታ፡፡

አቶ ፈቀደ ተፈራ «የአምላክ ልጆች ፋውንዴሽን» ከመሠረቱት አንዱ ናቸው፡፡ በአሁን ወቅት የቦርድ ሰብሳቢ ሆነው እያገለገሉ ይገኛሉ፡፡ የወላጆቹ የቅርብ ሰውም ናቸው፡፡ እርሳቸውን ጨምሮ ሌሎች ጎደኞቻቸው ሰብሰብ አሉ፡፡ የአምላክ ወላጆችን ለማጽናናት መምከር ጀመሩ፡፡ የልጃቸውን ስም ሊያስጠራ የሚችል ነገር ለማድረግ «ምን እናድርግ?» ብለው ተጨነቁ፡፡ ብቻ አንድ ነገር ማድረግ እንዳለባቸው ግን ወስነዋል። የአምላክ አባት ለሆኑት ለአቶ ፍቅር አለባቸው የልጃቸውን ስም ሊያስጠራ የሚችል ነገር ለመሥራት እንዳሰቡ ነገሯቸው።አባትም ልጃቸው ገና የ10 ዓመት እና የአራተኛ ክፍል ተማሪ እያለ ጽፎ ያስቀመጠው ራዕይ እንዳለ ተናገሩ፡፡ ልጃቸው ትምህርቱን ሲጨርስ ጎዳና ላይ ያሉ የሀገሩን ልጆች የመርዳት ራዕይ እንዳለው ጽፎ ነበር፡፡ አባትም ራዕዩን እንዲያሳካ የቻሉትን ሁሉ ሊያደርጉለት ቃል ገብተው ነበር፡፡ የአምላክ ባይኖርም አባት ግን ለቃላቸው ታመኑ፡፡

የአምላክ የቀብር ሥነ ሥርዓቱ ተፈጸመ፡፡ እነ አቶ ፈቀደም በቀብሩ ሥነ ሥርዓት ላይ በአምላክ ስም ድርጅት ለማቋቋም እንደታሰበ እና ለእዝን ተብሎ የሚወሰድ ውሃ፣ ቆሎ እና የመሳሰሉትን ከመስጠት ይልቅ ለሚመሠረተው ፋውንዴሽን ድጋፍ እንዲደርጉ የባንክ ሂሳብ ቁጥሩን በመንገር ይፋ አደረጉት፡፡

### የአምላክ ሀሳብ

ያሰቡትን ድርጅት ለማቋቋም ብዙ ውይይቶች እና ምክሮችን ማድረግ ጀመሩ፡፡ «ልጆች ጎዳና መውጣት የለባቸውም፡፡» የሚለውን የአምላክን ሃሳብ መሠረት በማድረግ «በአራት ምሰሶዎች ወይም ፒላርሶች ላይ መሥራት አለብን፡፡» በሚለው ሃሳብ ተስማሙ፡፡ ልጆች ወደ ጎዳና እንዲወጡ ከሚያደርጋቸው ምክንያቶቹ አንዱ ፍቺ ወይም የቤተሰብ መናጋት ነውና እዚህ ላይ መሥራት አለብን አሉ፡፡ ሴቶች በተለይም የኢኮኖሚ ችግር ካለባቸው ለተለያዩ ችግሮች ሲጋለጡ ይስተዋላል፡፡ እነርሱን ባሉበት በገንዘብ በስልጠና እና በሌላ መንገድ መደገፍ ላልተፈለገ እርግዝናም ሆነ ጎዳና ላይ እንዳይወጡ ያግዛል የሚለው ጉዳይ ሁለተኛ ሃሳብ ነው፡፡ ሦስተኛው ደግሞ ጎዳና የወጡት ልጆች ደግሞ ከቤተሰቦቻቸው ጋር የሚገናኙበትን ነገር እንፍጠር የሚል ይገኝበታል፡፡ አሁን አሁን ልጆቻቸውን ታቅፈው የሚለምኑ እናቶች እየተበራከቱ መጥተዋል፡፡ እነዚህን እናቶች «አራስ ቤት» ብለን እናቋቁማቸው በሚለው ሃሳብ ላይ ተስማሙ። «አራስ ቤት» የአምላክ ልጆች ፋውንዴሽን በማለት በ2012 ዓ.ም ፈቃድ አገኝቶ ሥራውን ጀመረ፡፡

ዘመድ አዝማድ ለሌላት እናት ከወለደች በኋላ ለእርሷ እና ለልጇ የሚያስፈልጋትን አልባሳት እና የንጽህና መጠበቂያ በማዘጋጀት ለጤና ጣቢያ በመስጠት በጎ ሥራውን ጀመረ፡፡ እንዲሁም ሆኖ አንዳንዶቹ ልጆቻቸውን ሆስፒታል ጥለው ይሄዳሉ። አንዳንዶቹ ደግሞ መጸዳጃ ቤት ይጥላሉ፡፡ የሚያርፉበት ቦታ አስፈልጎ ነበርና ቤት ተከራይተው «አራስ ቤት» ለብቸኛዋ እናት መጽናኛ ሆነ። አራሶች በቤታቸው እስከ ስድስት ወር ድረስ እንዲቆዩ ይደረጋል፡፡ እንደ ገንፎ፣ አጥሚት እና ሌሎች ምግቦችን እየወሰደች ራሷን እና ልጇን እንድትንከባከብ ትደረጋለች፡፡

ወደ አራስ ቤት የመጣች እናት ጎኗ ጠንከር እስኪል ለአንድ ወር ምንም አይነት ሥራ አትሠራም፡፡አንድ ወር ከሞላት በኋላ ግን ወደ ማእድ ቤት በመውጣት በፕሮግራሟ መሠረት ሥራዎችን ትሠራለች፡፡ ይህ ብቻ አይደለም፡፡ አራስ ቤት ያሉ እናቶች የነገ ሕይወታቸውን ምንም መምሰል እንዳለበት ይታሰብበታል፡፡ አራሶቹም ፍላጎታቸው ተጠይቆ በፍላጎታቸው መሠረት ስልጠና ይሰጣቸዋል፡፡ በአራስ ቤት ሁሉም ነገር የሚከወነው በፕሮግራም ነው፡፡ ለጨዋታ፣ ለሥራ፣ ለስልጠና እና ምግባቸውን የሚያበስሉት በፕሮግራማቸው መሠረት ነው፡፡ በየሳምንቱ ከሚመጡ በጎ ፈቃደኛ የሆኑ የሕክምና ባለሞያዎችም «እናት ደህና ልጅም ጤና» እንዲሆኑ የጤና ክትትል ይደረግላቸዋል፡፡

በተጨማሪም እናቶች ከአራስ ቤት የመውጫ ጊዜያቸው ሲደርስ ልጆቻቸው የቤተሰብ ፍቅር አግኝተው እንዲያድጉ ከልጃቸው አባት ጋር እርቅ እንዲወርድ ፋውንዴሽኑ የቻለውን ሁሉ ያርጋል። በተመሳሳይ ከቤተሰቦቻቸው ጋር እንዲታረቁ በማድረግ እና ወደ መጡበት አካባቢ የመቋቋሚያ እና የቀለብ ገንዘብ በመስጠት ሽኘት ይደረግላቸዋል።

በአጋዥነት ከነልጆቻቸው ተቀብሎ ቅጥር እንዲያገኙ ብሎም ልጆቹ የቤተሰብ ፍቅር እንዲያገኙ የቻለውን ሁሉ እየሠራ ይገኛል፡፡ ከቅጥር አኳያ ስልጠና ወስደው የልጆች ማቆያ ቦታዎች ላይ የተቀጠሩ እናቶች ይገኙበታል፡፡ የንግድ ክህሎት ላላቸው ደግሞ ከስልጠና በሻገር የሦስት ወር የቀለብ እና የኪራይ ይከፍልላቸዋል፡፡ ምንም እንኳን የሥራ ቦታ እጥረት ፈተና ቢሆንም የሚያስፈልጋቸውን ግብአቶችን ይሟላላቸዋል፡፡ ከአራስ ቤት ወጥተው በባልትና፣ ቡና ጠጡ፣ እንጀራ በመጋገር በሌች ሞያዎች ውጤታማ የሆኑ እናቶች አሉ፡፡ ትምህርታቸውን ያቋረጡ እናቶች ካሉም እንዲቀጥሉ ያደርጋል፡፡

የአምላክ ወላጆች ዛሬ ተጽናንተዋል፡፡ «ፈጣሪ የአምላክን ወስዶ ብዙ ልጆችን ሰጠን፡፡ » ይላሉ። የሆነባቸው ሁሉ ለመልካም እንደሆነ በማሰብ ብርታትን አግኝተዋል፡፡ ዛሬ የት ልሂድ ያለች፣ የተጨነቀች፣ ግራ የገባት አራስ እናትን ለማጽናናት ተችሏል፡፡ በአሁን ወቅት 24 እናቶች ከነልጆቻቸው እየታረሱ ይገኛል፡፡

ፋውንዴሽኑ 300 መቶ አባላት አሉት፡፡ ከአባላቱ ከሚገኘው ገንዘብ እና ከደጋፊ አካላት በሚያገኘው የገንዘብም ሆነ የዓይነት ድጋፍ የብዙ እናቶችን አብሷል። በርካታ ልጆችን ከጎዳና ሕይወት ታድጓል፡፡ አራስ ቤቱን ይህንን ሲያደርግ ግን ፈተናዎች አልገጡሙትም ማለት አይደለም፡፡ የቤት ኪራይ ክፍያ እና የኑሮ ውድነቱ ለድርጅቱ ተርፏል፡፡ የስኳር እና መሰል ምርቶችን ለማግኘት አዳጋች ሆኖበታል፡፡ ምሽት ላይ እናት ወይም ልጅ በድንገት ሲታመሙ የሚያወጣው የትራንስፖርት ገንዘብም ሌላኛው ፈተና ነው፡፡

ዛሬም ቢሆን ድጋፍ የሚሹ ብዙ ሴቶች አሉ፡፡ ፍላጎቱ ብዙ ቢሆንም ለሁሉም መድረስ ግን አዳጋች ሆኗል፡፡ እንዲህም ሆኖ እናቶችን ከሆቴሎች እና ከሌሎች ተቋማት ጋር በጋራ ለመሥራት ሙከራ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ አራስ ቤትን ከአዲስ አበባ ውጭ ለመሥራት ፍላጎት እና እቅድ አለ፡፡ ይህ የሚሳካው ግን ደጋፊ አካላት ድርጅቱን ሲደግፉ እና ሲያበረቱ ብቻ ነው፡፡

የዚህ ሁሉ በጎ ሥራ የአምላክ ፍቅር ራዕይ ነውና ከራዕዩ በእርሻ ስራ መሰማራት ዕቅድ አለው፡፡ ከእርሻ ከሚገኝ ገንዘብ ብዙዎችን ለመደገፍ የሚል ይገኝበታል። የእርሻ ቦታው ለማግኘት ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡ ከትምህርት አኳያም ለእናቶቹ መዋዕለ ሕጻናት በመክፈት ልጆቻቸውን እዛው በማስተማር ኑሯቸውን እንዲያቀኑ አቅዷል፡፡

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

**ሙሉጌታ ብርሃኑ**

አዲስ ዘመን ቀደም ባሉት ዓመታት እትሞቹ ከማኅደሩ ያስፈራቸው ብዙ ጉዳዮች ዛሬ ላይ ለትውልድ የሚሻገሩ ታሪክ ሆነው ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል ለትውስታ ያህል ቀንጭበን በ"አዲስ ዘመን ድሮ" ዓምዳችን በየሳምንቱ በጥቂቱ ማስታወሳችንን ቀጥለናል፡፡ ለዛሬ ከመረጥናቸው ርዕሰ ጉዳዮች መካከል፤ እድለኛዋ ባልቴት በተከታታይ ዓመታት የብሔራዊ ሎተሪ አሸናፊ ሆነው የተገኙበት ሚስጥሩ ምን ይሆን...በሀገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ የተማሪዎች የደንብ ልብስ ሲጀመር፤ የትጥቆቹ ዝርዝር ፈገግታም ግርምትንም የሚያጭሩ ናቸው፡፡ ወጣ ስንል ደግሞ አንድ አሕጉራዊና ሌላ ዓለም ዓቀፋዊ ጉዳዮችን እናገኝበታለን፡፡

### ያምናዋ ባለ 10 ሺህ ዘንድሮም 50 ሺህ አገኙ

የብሔራዊ ሎተሪ በተለይ ለእንቁጣጣሽ በዓል የተዘጋጀው የመጀመሪያው አንደኛ ዕጣ በሙሉ ለወይዘሮ ተዋበች ኪዳኔ ደርሷል፡፡

ወይዘሮ ተዋበች በአሁኑ ሎተሪ ሀምሳ ሺህ ብር ያገኙ ሲሆን፤ ባለፈው ዓመት የ10 ሺ ብር ዕድል ደርሷቸዋል፡፡

ዕድለኛይቱ የ59 ዓመት ወይዘሮ የስምንት ልጆች እናትና አያት ናቸው፡፡ ወይዘሮ ተዋበች በጠጅ ንግድ የሚተዳደሩ የይፋት ተወላጅ በአዲስ አበባ ሚያዚያ 27 አደባባይ ገደማ የሚኖሩ ናቸው፡፡

ወይዘሮ ተዋበች ይህንን ዕድል ያገኙት 37 ቲኬት ገዝተው ነው፡፡ በጠቅላላው ወይዘሮ ተዋበች ከ5 መቶ በላይ ቲኬት መግዛታቸውን ገልጸዋል፡፡ ያሁኑም 50 ሺህ ብር የደረሳቸው የአንድ አይነት ቁጥር ሙሉ ሴሪ በመግዛታቸው ነው ሲል የብሔራዊ ሎተሪ አድሚንስትሬሽን ጽ/ቤት ገልጧል፡፡

(አዲስ ዘመን መስከረም 7 ቀን 1957 ዓ.ም)

### ተማሪዎች በታኅሣሥ ወር የመለያ ልብስ ይኖራቸዋል

የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች፤ ወንዶችም ሴቶችም የትምህርት ቀን ልብስ እንዲለብሱ የሚል ሕግ የትምህርትና የሥነ ጥበብ ሚኒስቴር ስላወጣ፤ ሕጉ ከዚህ ዓመት ጀምሮ በሥራ ላይ እንደሚውል አቶ ዓምደ ሚካኤል ሀብቴ የትምህርት ሚኒስቴር ማስታወቂያ ክፍል ሹም ገልጠዋል፡፡

...

ለአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች ለወንዶች አንድ ቦላሌ ሱሪ፤ አንድ ቁምጣ ሱሪ፤ አንድ ሸሚዝና አንድ ኮት ዋጋው በጠቅላላው 9.80(ዘጠኝ ብር ከሰማኒያ ሳንቲም) ለአንደኛ ደረጃ ሴቶች ተማሪዎች፤ አንድ ቀሚስ፤ አንድ ሸሚዝ(ብላውዝ) አንድ የውስጥ ሱሪ( ሙታንታ) ዋጋው በጠቅላላው 6.65 (ስድስት ብር ከስድሳ አምስት ሳንቲም) ነው፡፡

ለሁለተኛ ደረጃ ወንዶች ተማሪዎች አንድ ቦላሌ፤ አንድ ቁምጣ፤ አንድ ሸሚዝና አንድ ኮት ዋጋው በጠቅላላው 13.20 (አሥራ ሦስት ብር ከሃያ ሳንቲም) ለሁለተኛ ደረጃ ሴቶች ተማሪዎች አንድ ቀሚስ፤ አንድ ሸሚዝና አንድ የውስጥ ሱሪ (ሙታንታ) ዋጋው በጠቅላላው 8.96 (ስምንት ብር ከዘጠና ስድስት ሳንቲም) እንደሚሆን ወሬው በተጨማሪ አስገንዝቧል።

...

የግልና የሚሲዮን ትምህርት ቤቶች፤ ከትምህርትና ከሥነ ጥበብ ሚኒስቴር ጋር በመስማማት ተማሪዎቻቸው ዩኒፎርም እንዲኖራቸው ሳይደረግ እንደማይቀር በተስፋ ይጠበቃል ሲሉ አቶ ዓምደ ሚካኤል አስረድተዋል፡፡

(አዲስ ዘመን መስከረም 13 ቀን 1957 ዓ.ም)

### የአጭር ቀሚስ ቁጥጥር በሐረር

**ሐረር፡ (ኢ-ዜ-አ-)** በሐረር ከተማ ውስጥ አጫጭር ቀሚስ እየለበሱ በሚዘዋወሩት ሴቶች ላይ ጥብቅ ቁጥጥር እየተደረገ መሆኑን የሐረር አውራጃ ፖሊስ አዛዥ ሌተናል ኮሎኔል ኃይለሚካኤል ገብሬ ገለጡ፡፡

በተደረገው ቁጥጥር መሠረት በሐረር ከተማ ውስጥ የሀገርን ባሕል የሚያጎድፍ ልብስ ለብሰው የተገኙት 67 ልጃገረዶችና ሴቶች 2ኛ ፖሊስ ጣቢያ እየቀረቡ ዳግመኛ ላለመልበስ መፈረማቸውን ሌተናል ኮሎኔል ኃይለ ሚካኤል አስረድተዋል፡፡

ይኸው አፈጻጸም ለወደፊቱ በየጣቢያው ተላልፎ በሚገባ በሥራ ላይ እንደሚውል ታውቋል፡፡

በዚሁ ይዞታ በከተማው ውስጥ ይታይ ነበረው የአጭር ቀሚስ ለባሾች ቁጥር መቀነሱንና ለወደፊት ጨርሶ እንደሚጠፋ ሌተናል ኮሎኔል ኃይለሚካኤል ገብሬ እምነታቸው መሆኑን ገልጠዋል፡፡

(አዲስ ዘመን ጥቅምት 2 ቀን 1962 ዓ.ም)

### ልጃገረዷ በጥፊ ስለተመታች የኩባንያው ሠራተኞች አንሠራም አሉ

ከሌጎስ፤ በናይጄሪያ ውስጥ የሚገኘውን የኪንግስዌይ ግምጃ ቤት ሥራ ይመራ የነበረው እንግሊዛዊው፤ የግምጃ ቤቱ የሽያጭ ክፍል ሠራተኛ የነበረችውን አንዲት ልጃገረድ በጥፊ ስለመታት፤ ይህ ሰው ከሥራው ካልተወገደ በማለት በግምጃ ቤቱ ውስጥ ይሠሩ የነበሩት አንድ ሺህ ናይጄሪያውያን ሠራተኞች ሥራቸውን አቁመዋል፡፡

የግምጃ ቤቱ ባለንብረት የሆነው የተባበረው የአፍሪካ ኩባንያ የሠራተኞች አንድነት ኤክስኪዩቲቭ፤ ባለፈው ሳምንት መጀመሪያ ላይ፤ የናይጄሪያዋን ልጃገረድ አደገኛ ጥፊ የመታት የብሪታኒያው ተወላጅ ሚስተር ፒተር ቻድዊክ ከሥራው እንዲወጣ የተጠየቀ መሆኑንና በሚመጣው ቅዳሜ ናይጄሪያን ለቅቆ ይወጣል ሲል አስታውቋል፡፡

የግምጃ ቤቱ የወሬ ምንጭ፤ ሚስተር ፒተር ቻድዊክ የልጃገረዷን ትከሻ መታ በማድረግ በደንብ እንድትሠራ አሳስቧታል ሲል ገልጧል፡፡

በመቶ የሚቆጠር ፖሊስ ግምጃ ቤቱን ከብቦ እንደነበር ወሬው ሲያመለክት፤ እስካሁን አደጋ ያልደረሰ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

(አዲስ ዘመን ኅዳር 26 ቀን 1957ዓ .ም)

### ቦንቡን ዕብድ እንዳይተኩሰው ጥንቃቄ ተደርጓል

ቢትል፤ አንድ አዕምሮው ትክክል ያልሆነ ሰው በድንገት ተነስቶ የኒውክሌር ጦር መሣሪያዎችን ቃታ በመሳብ ዓለምን ከአደገኛ ሁኔታ ላይ እንዳይጥል አሜሪካ ጥብቅ ቁጥጥር ታደርጋለች ሲሉ፤ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት በአንድ የእራት ግብዣ ላይ ተናግረዋል፡፡

...

የኒውክሌር ጦር መሣሪያዎች እንዲተኮሱ የሚያዘው ፕሬዚዳንቱ ብቻ ነው፡፡ ከእርሱም ጋር ሁለት ወይም ሦስት ሰዎች ይመካከራሉ፡፡

...

መሣሪያዎቹም የኤሌክትሮኒክስ ቁልፎች ይገኙባቸዋል፤ እነዚህንም ቁልፎች ለመፍታት የሚቻለው በምስጢራዊ ዘዴ ነው፡፡ ይህንንም አያያዛችንን በጥብቅ እንከታተላለን ሲሉ መናገራቸውን ሮይተር ገልጧል፡፡

(አዲስ ዘመን የካቲት 13 ቀን 1957 ዓ.ም)

# ዓለም አቀፍ

## በሞስኮው ጥቃት ተሳታፊ ናቸው የተባሉት ላይ ክስ ተመሠረተ

ሩሲያ በሞስኮ የሙዚቃ ዝግጅት 137 ሰዎችን ገድለዋል ባለቻቸው 4 ግለሰቦች ላይ ክስ መሠረተች። ሦስቱ ተጠርጣሪዎች በፖሊስ ተጠፍንገው አንዱ ደግሞ ተሽከርካሪ ወንበር ላይ ሆኖ ፍርድ ቤት ከቀረቡ በኋላ የሽብር ክስ ተመስርቶባቸዋል። ባሳለፍነው ዓርብ መጋቢት 13 ቀን 2016 ዓ.ም. አራት ግለሰቦች በፈጸሙት ጥቃት 137 ሰዎችን መገደላቸው ይታወሳል።

ለዚህ ጥቃት እስላሚክ ስቴት ወይም አይኤስ ኃላፊነቱን ወስዶ ጥቃት አድራሾቹ ጥቃቱን ሲያደርሱ የሚያሳይ ምስል ለጥፏል። የሩሲያ ባለሥልጣናት ምንም አይነት ማስረጃ ሳያቀርቡ ዩክሬን በዚህ ጥቃት ተሳታፊ ሆናለች ብለዋል። ዩክሬን በጥቃቱ አለመሳተፏን ገልጻ ከሩሲያ የቀረበባትን ክስ አጣጥላለች።





በሞስኮ ጥቃት ተጠርጣሪዎች፣

በጥቃቱ በመሳተፍ በሽብር ክስ የተመሠረተባቸው ግለሰቦች ዳሌርደዘሆን ሚረዞዬቭ፣ ሳኢዳካራሚ ሙሮዳሊ ራቻባሊዞዳ፣ ሻመሰዲን ፋሪዱኒ እና ሞሐማዳሶቢር ዳይዞቭ ናቸው። አራቱም ፍርድ ቤት ሲቀርቡ አካላዊ ጉዳት እንዳለባቸው ይታያል።

የሁለቱ ተከሳሾች ዓይን ጠቁሮ የሚታይ ሲሆን የሌላኛቸው ተከሳሽ ጆሮ እንዲሁም አንገቱ በፕላስቲክ ተጠቅልሎ ነበር። በተሽከርካሪ ወንበር የመጣው ተከሳሽ አንድ ዓይኑን ማጣቱን ሮይተርስ የዜና ወኪል ዘግቧል። በቴሌግራም ቻናል ላይ የወጣ የፍርድ ቤት መግለጫ የታጃኪስታን ዜጋ የሆነው ሚራዞዬቭ እንዲሁም ራቻባሊዞዳ ጥፋተኛ መሆናቸውን አምነዋል ይላል።

በዚህ ጥቃት ክስ የተመሠረተባቸው እነዚህ አራት ግለሰቦች ጥቃቱ ከተፈጸመ ከአራት ሰዓታት በኋላ ነበር በቁጥጥር ስር የዋሉት። አራቱ ተጠርጣሪዎች ወደ አዳራሹ በመግባት ያገኙት ሰው ላይ በዘፈቀደ በመተኮስ ባደረሱት ጥቃትም ከገደሏቸው 137 ሰዎች በተጨማሪ 140 ሰዎች ላይ ጉዳት አድርሰዋል።

ባለሥልጣናት እንደገለጡት በጠቅላላው 11 ሰዎች በቁጥጥር ሥር መዋላቸውን እና አራቱ ተጠርጣሪዎች ወደ ዩክሬን ድንበር ሲያቀኑ ነው የተያዙት ብለዋል። ሩሲያ አይኤስ ለጥቃቱ ኃላፊነት ስለመውሰዱ እስካሁን ያለችው ነገር የለም። ይልቅ በዚህ ጥቃት ዩክሬን ተሳታፊ ስለመሆኗ ጠቁመዋል።

ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን ታጣቂዎቹ የተያዙት ወደ ዩክሬን ለማምለጥ ሲሞክሩ ነበር ብለዋል። ዩክሬን በጥቃቱ እጇ አለበት የተባለውን ክስ አስተባብላ "የማይመስል ነገር ነው" የሚል አስተያየት ሰጥታለች። ይህ ጥቃት ከመፈጸሙ ከሳምንታት ቀድሞ በሞስኮ የሚገኘው የአሜሪካ ኤምባሲ በመዲናዋ የሽብር ጥቃት ሊፈጸም እንደሚችል ማሳሰቢያ አውጥታ ነበር።

ነገር ግን የሩሲያ መንግሥት ይህን ማስጠንቀቂያ በወቅቱ በሩሲያ ምርጫ ጣልቃ ለመግባት የሚደረግ "ፕሮፖጋንዳ ነው" በሚል አጣጥሎታል። ከዚህ ጥቃት በኋላ አሜሪካ ይህን ጥቃት ያደረሰው አይኤስ ስለመሆኑ ምንም ጥርጣሬ የለኝም ብላለች።

አይኤስ ሩሲያን ዒላማ ያደረገ ጥቃት ሲፈጽም ይህ የመጀመሪያው አይደለም። እአአ 2015 ላይ ከግብፅ ወደ ሩሲያ በሚበር አውሮፕላን ላይ ቦምብ ጠምዶ አብዛኛዎቹ የሩሲያ ዜጎች የሆኑ 224 ሰዎችን ገድሎ ነበር። እአአ 2017 ላይ ደግሞ አይኤስ በሩሲያዋ ሴንት ፒተርስበርግ ከተማ ባቡር ጣቢያ ላይ የቦምብ ጥቃት ፈጽሞ 15 ሰዎችን ገድሏል።

የደኅንነት ተንታኞች እንደሚሉት ከሆነ አይኤስ ሩሲያን ዒላማ አድርጎ ከያዘባቸው ምክንያቶች ዋነኛ በሶሪያ በነበራት ተሳትፎ ነው። ሩሲያ ከኤይኤስ ጋር ሲዋጉ የቆዩት የበሽር አላ-አሳድ አስተዳደርን ለማስቀጠል ድጋፍ አድርጋለች እንዲሁም አይኤስ ከሶሪያ እንዲወጣ ትልቅ ወታደራዊ ሚና ተጫውታለች ማለታቸውን ቢቢሲ ዘግቧል።

## በሴኔጋል በፕሬዚዳንታዊ ምርጫ የተቃዋሚው ፓርቲ መሪ የአሸናፊነት ግምት ተሰጣቸው


በሴኔጋል በተካሄደው ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ የተቃዋሚው ፓርቲ መሪ ባሲሩ ዲዮማዬ ፋዬ አሸናፊ እንደሚሆኑ ግምት ተሰጠ። በርካታ ተቀናቃኞች ሽንፈታቸውን አምነው መቀበላቸውም ተሰምቷል።

ከሦስት ዓመታት አለመረጋጋት እና በሥልጣን ላይ በነበሩት ማኪ ሳል ላይ የተነሳውን ተቃውሞ ተከትሎ ሚሊዮኖች እሑድ በተደረገው ሠላማዊ ምርጫ ተሳትፈዋል። ለፕሬዚዳንትነት 19 እጩዎች በምርጫው ቀርበው ነበር።

የገዢው ፓርቲ ተወካይ አማዱ ባ ተሸንፈዋል የሚሉ ሪፖርቶችን ውድቅ በማድረግ አሸናፊውን ለመወሰን ሁለተኛ ዙር ምርጫ ይካሄዳል ብለው እንደሚጠብቁ ተናግረዋል። የ44 ዓመቱ ፋዬ ከምርጫው በፊት ታስረው በነበሩት በኡስማን ሶንኮ የሚመራው የፓስቴፍ ፓርቲ አባል ናቸው። ሶንኮ በቀረበባቸው የስም ማጥፋት ክስ ከውድድሩ ውጭ እንዲሆኑ ተደርጓል።

በቴሌቪዥን በታወጀው የመጀመሪያው ውጤት ፋዬ አብላጫ ድምጽ ማግኘታቸው ሲነገር በዋና ከተማዋ ዳካር ጎዳናዎች ላይ በርካቶች ደስታቸውን ገልጸዋል። ደጋፊዎቹ ርችቶችን ሲተኩሱ፣ የሴኔጋልን ባንዲራ ሲያውለበልቡ እና ቩቩዜላዎችን ሲነፉ ታይተዋል።

ውጤቱን ተከትሎ አምስት የተቃዋሚ ፓርቲ እጩዎች ፋዬን አሸናፊ አድርገው አውጀዋል። አንታ ባባካር ንጎም ከፍተኛ ግምት ካገኙ እጩዎች አንዱ የነበሩ ሲሆን ባወጡት መግለጫ ለፋዬ ስኬትን ተመኝተዋል። ሌላኛው ተቀናቃኝ ሶንኮ እንዲሁ ፋዬን ደግፈዋል።




የወቅቱ ፕሬዚዳንት ማኪ ሳል በዚህ ፕሬዚዳንታዊ ውድድር ተሳታፊ ሳይሆኑ ቀርተዋል። ይህን በሴኔጋል ታሪክ በእጩነት ያልቀረቡ በሥልጣን ላይ ያሉ የመጀመሪያው ፕሬዚዳንት አድርጓቸዋል።

ፕሬዚዳንቱ የሚመሩት የገዥ ፓርቲያቸው ጥምረት የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር የ62 ዓመቱን ባ እጩ አድርጎ አቅርቦ ነበር። የባ የምርጫ ቅስቀሳ ቡድን "ከእኛ ባለሙያዎች ቡድን የተገኘውን ውጤት ከግምት ውስጥ በማስገባት በጣም ከከፋ ወደ ሁለተኛ ዙር ምርጫ እንደምንሄድ እርግጠኞች ነን" ብሏል።

ሴኔጋል ወደ 18 ሚሊዮን የሚጠጋ ሕዝብ ያላት ሲሆን ከዚህ ውስጥ 7 ነጥብ 3 ሚሊዮን ሰዎች ድምፅ ለመስጠት ተመዝግበዋል። እስካሁን ከ15 ሺህ 633 የምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ ምን ያህሉ እንደተቆጠሩ ግልጽ አይደለም። የመጨረሻ የምርጫ ውጤቶች ዛሬ ማክሰኞ እንደሚጠበቁ የቢቢሲ ዘገባ አመልክቷል።

# ስፖርት




# በዓለም ሃገር አቋራጭ ቻምፒዮና የሚሳተፈው ቡድን ዛሬ ይሸኛል

**ብርሃን ፈይሳ**

የዓለም ሃገር አቋራጭ ቻምፒዮና ከጥቂት ቀናት በኋላ በሰርቢያ ቤልግሬድ ይካሄዳል፡፡ ዘንድሮ ለ45ኛ ጊዜ በሚካሄደው በዚህ የዓለም ሃገር አቋራጭ ቻምፒዮና ላይ የሚካፈለው የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ቡድንም የሀገር ውስጥ ዝግጅቱን አጠናቆ ዛሬ ምሽት ሽኝት እንደሚደረግለት የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን አስታውቋል፡፡

እአአ ከ1973 አንስቶ ሳይቋረጥ እየተካሄደ አሁን ካለበት ደረጃ የደረሰው ይህ ቻምፒዮና በ5 የውድድር ዓይነቶች በመጪው ቅዳሜ መጋቢት 22/2016 ዓ.ም ይካሄዳል፡፡ በ10ኪሎ ሜትር አዋቂ፣ በ8እና6 ኪሎ ሜትር ወጣቶች እንዲሁም ድብልቅ ሪሌ፤ ከ51 የዓለም ሃገራት የተወጣጡ 485 አትሌቶችን ያሳትፋል፡፡ በአንጋፋው አትሌት መሃመድ ከድር የብር ሜዳሊያ የጀመረው የኢትዮጵያ የሃገር አቋራጭ ቻምፒዮና ውጤታማ ጉዞም እንደ ቀነኒሳ በቀለ ያሉ በውድድሩ ትልቅ ታሪክ የሰሩ አትሌቶችን በማፍራት ቀጥሏል። በረጅም ርቀት አትሌቲክስ ስኬታማ ከሆኑት ሃገራት መካከል የምትመደበው ኢትዮጵያ በዚህ ውድድር በግልም ሆነ በቡድን የበላይነት ከሚጠበቁ ጠንካራ ሀገራት መካከል አንዷ ናት፡፡

የዘንድሮው የኢትዮጵያ የሃገር አቋራጭ ቻምፒዮና ብሄራዊ ቡድንም ዝግጅቱን አጠናቆ የውድድሩን መጀመር ብቻ በመጠባበቅ ላይ ይገኛል፡፡ ኢትዮጵያን በዚህ ዓለም አቀፍ መድረክ የሚወክሉ አትሌቶች በጃንሜዳ ኢንተርናሽናል ሃገር አቋራጭ ቻምፒዮና የተመረጡ ሲሆን፣ ከወር በፊት በቱኒዚያ በተካሄደው የአፍሪካ ሃገር አቋራጭ ቻምፒዮናም ጠንካራ ተፎካካሪ በመሆን አቅሙን ማሳየት ችሏል፡፡



**የሃገር አቋራጭ አትሌቲክስ ቡድን በሰርቢያ ውጤታማ የሚያደርገውን ዝግጅት ሲያደርግ ቆይቷል፤**

14 ሴት እና 14 ወንድ በአጠቃላይ 28 አትሌቶችን ያቀፈው የኢትዮጵያ የሃገር አቋራጭ ቡድን፤ ከየካቲት 28/2016 ዓ.ም ጀምሮ ልምምዱን ሲያከናውን ቆይቷል። በረጅም ጊዜ የቻምፒዮናው ተሳትፎ ባስቆጠረቻቸው ሜዳሊያዎች ከዓለም ሁለተኛ ደረጃ ላይ የምትገኘው ኢትዮጵያ፤ ክብሯን አስጠብቃ በስኬታማነት ለመመለስ የሚያስችሉ አትሌቶችም በቡድን ስብስቡ ተካተዋል፡፡

በሃገር አቋራጭ ቻምፒዮና በርካታ ሜዳሊያዎችን በመሰብሰብ ቀዳሚ የሆነችው ጎረቤት ሃገር ኬንያ የኢትዮጵያውያን አትሌቶች ቀዳሚ ተፎካካሪ ስትሆን፤ የኡጋንዳ አትሌቶችም ቀላል ግምት የሚሰጣቸው አይደሉም፡፡ በተለይ ባለፈው ዓመት በባትረስ በተካሄደው ቻምፒዮና በአዋቂ ወንዶች የወርቅና የነሃስ ሜዳሊያ ያጠለቁት ኡጋንዳውያን ጃኮብ ኪፕሊሞ እና ጆሹዋ ቺፕቴጊ ሜዳሊያውን በድጋሚ ወደሃገራቸው መመለስን ዓላማ ማድረጋቸውን የዓለም አትሌቲክስ ዘገባ ያሳያል፡፡ ይሁንና የወርቅ ሜዳሊያው አምና በጥቂት ሰከንዶች ልዩነት ተበልጦ የብር ሜዳሊያ ለማጥለቅ ከተገደደው ወጣቱ ኢትዮጵያዊ አትሌት በሪሁ አረጋዊ እጅ የሚወጣ አይመስልም፡፡ አትሌቱ በውድድር ዓመቱ ተሳትፎው ምርጥ አቋም ላይ የሚገኝ መሆኑን ተከትሎ የወንዶች 10 ኪሎ ሜትር ፉክክሩ ከወዲሁ ተጠባቂ እንዲሆን አስችሎታል፡፡

በድብልቅ ሪሌ ከሚሳተፉ 12 ሃገራት መካከል አንዷ የሆነችው ኢትዮጵያ እንደተለመደው ሜዳሊያ የማግኘት እድሏ ከፍተኛ እንደሚሆን ይጠበቃል፡፡ በዚህ ቡድን ውስጥ ከተካተቱ አትሌቶች አንዱ የሆነው ሃጎስ ገብረህይወት ደግሞ የበርካቶችን ትኩረት ስቧል። በሪጋ የጎዳና ላይ ቻምፒዮና እንዲሁም ከቀናት በፊት በጋና አክራ የአፍሪካ ጨዋታዎች ላይ በ5ሺ ሜትር የወርቅ ሜዳሊያ ለሃገሩ ማስመዝገብ የቻለው ሀቦስ ሰርቢያ ላይ የወርቅ ሜዳሊያ ያጠልቃል ተብሎ ተስፋ ተጥሎበታል፡፡

ከ20 ዓመት በታች ወጣቶች በሚደረገው ውድድርም አምና አውስትራሊያ ላይ ተሳትፈው ልምድ ማግኘት የቻሉት በሴት ለምለም ንብረት፣ በወንዶች ደግሞ አቤል በቀለን የመሳሰሉ ወጣት አትሌቶችም በቤልግሬድ በድጋሚ የሚታዩ መሆናቸውን ተከትሎ በግላቸው ሜዳሊያ የማስመዝገብ ግምትም አግኝተዋል።

በዚህ ቻምፒዮና በርካታ ሜዳሊያዎችን በማግኘት በወንዶች ቀነኒሳ በቀለ፤ በሴቶች ደግሞ ደራርቱ ቱሉ እና ጥሩነሽ ዲባባን የመሳሰሉ አትሌቶች መጥቀስ ይቻላል፡፡ እንደ ሃገር ሲታይ ደግሞ ኢትዮጵያ ኬንያን በመከተል 107 የወርቅ፣ 115 የብር እና 63 የነሃስ በጥቅሉ 285 ሜዳሊያዎችን በማስቆጠር ሁለተኛ ደረጃ ላይ ተቀምጣለች፡፡ አምና በአውስትራሊያዋ ባትረስ በተካሄደው ውድድር ኢትዮጵያ 2 የወርቅ፣ 7 የብር እና 1 የነሃስ በድምሩ 10 ሜዳሊያዎችን ማግኘቷ የሚታወስ ነው፡፡

## የጨረታ ማስታወቂያ

የጉምሩክ ህግን ተላልፎ የተያዙ የተለያዩ የኮንትሮባንድ እቃዎች ዓርብ መጋቢት 20 ቀን 2016 ዓ/ም በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ ለመሸጥ ይፈልጋል። በመሆኑም በጨረታው መሳተፍ የምትፈልጉ ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን ከአዋሽ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት በመግዛትና ለጨረታ የቀረቡትን የእቃዎችን ዝርዝር ከጨረታ ሰነዱ በማየትና እና በማረጋገጥ የሚከተሉትን ዝርዝር መስፈርቶች በማሟላት ከታች በጨረታው መሳተፍ የምትችሉ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**የጨረታ መስፈርቶች፡-**

1. ለጨረታ በቀረቡት ዕቃዎች ላይ ለመሳተፍ የሚያስፈልጉ ተጫራች በጨረታ በሚሸጡ ዕቃዎች ጋር በዘርፉ የታደሰ ንግድ ፍቃድ፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ሰርተፍኬት፣ የዘመኑን ግብር የከፈለ ስለመሆኑ ክሊራንስ (Clearance) እና የተጨማሪ እሴት ታክስ እንቅስቃሴያቸውን ለታክስ ማዕከሉ ያሳወቁበት በቅርብ ጊዜ የተሰጣቸው የምስክር ወረቀት እና የመለያ ቁጥሩን ከመጫረቻ ሰነዱ ጋር አያይዞ ማቅረብ የሚችል።

2 ተጫራቾች የጨረታውን ሰነድ ዘወትር በስራ ሰዓት እስከ ዓርብ 20/07/2016 ዓ/ም ባሉት ቀናት ለግልጽ ጨረታ እስከ ጠዋቱ 3:45 እንዲሁም ለሐራጅ ጨረታ የግልጽ ጨረታ እንደተጠናቀቀ እስከ ረፋዱ (ጠዋቱ) 5:00 ሰዓት የእቃውን ዝርዝር የያዘ የጨረታው ሰነድ ከአዋሽ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ገቢ አሰባሰብ ቢሮ የማይመለስ ብር 100.00 /አንድ መቶ ብር / በመክፈል መግዛት ይችላሉ ።

3. ለግልጽ ጨረታ ለመሳተፍ ተጫራቾች ለጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና (cpo) ብር የሚወዳደሩበት እቃ ኮድ 5 በመቶ እንዲሁም ለሐራጅ ጨረታ ለሚወዳደሩበት እቃ ኮድ ብር 100,000 (አንድ መቶ ሺህ ብር) በባንክ አሰርተው በአዋሽ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ስም ማስያዝ ይኖርባቸዋል፡፡

4. ተጫራቾች በሚከተለው የጨረታ ቀናት (እስኬጁል) መሰረት በአዋሽ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት በመገኘት መጫረት ይችላሉ።

| ተ.ቁ | የጨረታ ቦታ | የጨረታ ዓይነት | ለጨረታ የቀረቡ እቃዎች | የዕቃዎች መመልከቻ ቀን በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ | የጨረታው የመዝጊያ እና የመከፈቻ ቀንና ሰዓት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | አዋሽ ጉምሩክ | ግልጽ | የእጅ ሰዓቶች፣ የእጅ ባትሪዎች፣ ብዛት ያላቸው የሴቶች የእጅ ቦርሳ የተለያዩ አርተፊሻል ጌጣጌጦች እንዲሁም የሴቶች የጸጉር ማስያዣ እና የጸጉር ትያራ | ዓርብ 20/07/16 ዓ/ም እስከ ጠዋቱ 3፡45 ሰዓት | ዓርብ 20/07/16 ዓ.ም እስከ ጠዋቱ 4፡00 ሰዓት |

5. የጨረታው መክፈቻ ቦታ በአዋሽ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት የሚካሄድ ሲሆን ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው ባሉበት ወይም በታዛቢዎች ፊት ይከፈታል።

6. ለጨረታው አሸናፊ ተጫራቾች ለጨረታው ዋስትና ያስያዙት (cpo) ከሚከፍሉት ዋጋ ጋር የሚታሰብላቸው ሲሆን ለተሸናፊ ተጫራቾች ደግሞ የጨረታ ውጤት ከተለጠፈበት ቀን ጀምሮ በ3 የስራ ቀናት ውስጥ ተመላሽ ይደረግላቸዋል።

7 ከአሸናፊ ተጫራቾች ማሸነፋቸው በደብዳቤ ከተገለጸላቸው ቀን ጀምሮ በ3 ቀናት ውስጥ ያሸነፈበትን ገንዘብ ገቢ በማድረግ ዕቃውን በመረከብ ከመጋዘን ማውጣት ይኖርበታል።

8. ከላይ በተ.ቁ.7 በተገለጹት ቀናት ውስጥ ክፍያውን ገቢ ያላደረጉ እና ንብረቱን ተረክበው ያልወሰዱ ተጫራቾች ለጨረታው ማስከበሪያ ያስያዙት ገንዘብ እና ለንብረቱ የከፈሉት ዋጋ ለኮሚሽኑ ገቢ ሆኖ ዕቃው በድጋሚ ለሽያጭ ይቀርባል፡፡

9. ቅ/ጽ/ቤቱ ጨረታውን በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።

**ለተጨማሪ መረጃ በስልክ ቁጥር-022-224-1402 ደውለው ስለ ጨረታው መረጃ መጠየቅ ይቻላል።**

**የአዋሽ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት**